# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 151 የካቲት 1 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




## አቶ ተመስገን ጥሩነህ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ

- አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ የውጭ ጉዳይ፤ ዶክተር መቅደስ ዳባ የጤና ሚኒስትር በመሆን ቃለመሃላ ፈጽመዋል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው ስብሰባ አቶ ተመስገን ጥሩነህን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ሲሾም የሁለት ሚኒስትሮችንም ሹመት አጽድቋል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 15ኛ መደበኛ ስብሰባ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በእጩነት የቀረቡትን አቶ ተመስገን ጥሩነህን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣


አቶ ተመስገን ጥሩነህ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




## የአምቦ - ወሊሶ

## መንገድ ግንባታ ከዘጠኝ ዓመት በላይ በመጓተቱ መቸገራቸውን ነዋሪዎች ገለጹ

-የአካባቢው አመራሮች መንገዱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ብለዋል


ገጽ 6




## ኢትዮጵያ

## ‘የብሪክስ አዲስ የልማት ባንክ‘ን እንድትቀላቀል አባል ሀገራቱ ድጋፍ እያደረጉ ነው


ገጽ 6


## ረጂ ተቋማት ርዳታ ካቋረጡ በኋላ መንግሥት ለሰብዓዊ ድጋፍ 11 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር አውጥቷል

-ለ6 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዜጎች ርዳታ ለመስጠት ዝግጅት ተደርጓል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ረጂ ተቋማት ርዳታ ካቋረጡ በኋላ መንግሥት ለሰብዓዊ ድጋፍ 11 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ወጪ ማድረጉን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ በአራተኛ ዙር ለ6 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ እንዳለም ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አታለለ አቡሀይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት ረጂ ተቋማት ሥራቸውን አቋርጠው ከወጡ ጀምሮ መንግሥት 11 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ወጪ በማውጣት ለዜጎች ሰብዓዊ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ሌሎች ረጂ ተቋማትን በማስተባበር ደግሞ 4 ቢሊዮን ብር እንዲለግሱ ተደርጓል፡፡

እንደ ከፍተኛ ባለሙያው ገለፃ፤ ተቋሙ ለተረጂዎች ድጋፍ ለማድረግ ሁልጊዜም ዝግጁ ነው፡፡ በመላው ሀገሪቱ


ረጂ ተቋማት ርዳታ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





AfriSky PLC
ETHIOPIA
REBAR
WIREROAD
RHS
TANKER
NAIL
0940 80 80 80 | 0940 90 90 90 | 0911 21 72 55 | 0940 50 50 50

AMG STEEL FACTORY
ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory

# የብዝሃ ሳተላይት መረጃ መቀበያ ጣቢያ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ አገልግሎት መስጠት ጀመረ

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- የብዝሃ ሳተላይት መረጃ መቀበያ ጣቢያ መረጃዎችን ለሀገራትና ድርጅቶች በመሸጥ የውጭ ምንዛሬ ማስገባት የሚያስችል አገልግሎት ማስጀመሩን የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

ኢንስቲትዩቱ አገልግሎቱ በይፋ መጀመሩን ምክንያት በማድረግ ለከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች እና የሚዲያ ባለሙያዎች በእንጦጦ ኦብዘርቫቶሪና ምርምር ማዕከል ገለጻ አድርጓል፡፡

በወቅቱ የክብር እንግዳ ሆነው አገልግሎቱን በይፋ ያስጀመሩት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ይሽሩን አለማየሁ፤ ኢንስቲትዩቱ በሳይንስ ዘርፉ ተጨባጭ እድገት እንዲታይ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት በርካታ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ጣቢያውን በመጠቀም የሳተላይት አገልግሎት ለሀገራትና ለድርጅቶች በመስጠት ኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ የምታገኝበት ሁኔታ መፍጠሩ የሚያስመሰግን ነው ብለዋል፡፡

የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዲሳ ይልማ እንዳብራሩት፤ የብዝሃ ሳተላይት መረጃ መቀበያ ጣቢያ በ2013 ዓ.ም ተገንብቶ ወደ ሥራ የገባ ሲሆን፤ እስካሁንም የሚያገኛቸውን የሳተላይት መረጃዎች ለሀገር ውስጥ አገልግሎት ሲያውል መቆየቱን ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅትም የብዝሃ ሳተላይት መረጃ መቀበያ ጣቢያው 'ግራውንድ ሳተላይት አስ ኤ ሰርቪስ' የተሰኘ አገልግሎት በማስጀመር የተለያዩ ሀገራትና ድርጅቶች ኢትዮጵያ ባላት የመሬት መረጃ መቀበያ ጣቢያ አማካኝነት ከሳተላይቶች መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡

አገልግሎቱ የመሬት መረጃ መቀበያ ጣቢያ ለሌላቸው እንዲሁም ጣቢያ ኖሯቸው ተደራሽነታቸው ሰፊ ላልሆኑ ሀገራት እና ድርጅቶች የሚሰጥ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ አብዲሳ ገለፃ፤ የመረጃ መቀበያ ጣቢያው አገልግሎት ለሚፈልጉ ድርጅቶች እና ሀገራት ሳተላይቶቻቸው በሚያልፉበት ብዛት ወይም በተጠቀሙበት ደቂቃ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ነው፡፡ በዚህ የመሬት የመረጃ መቀበያ ጣቢያ አገልግሎት መስጠት ሥራ ከ10 በላይ ሳተላይቶችን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ጣቢያው ከሳተላይቶች ከፍተኛ ጥራት ያለው መረጃ ከመቀበል ባሻገር የገበያ እድሎችን በመፍጠር የውጭ ምንዛሬ ማስገባት ደረጃ ላይ ደርሷል ያሉት አቶ አብዲሳ፤ ጣቢያው ምሥራቅ አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ የሚያካልልና መረጃዎችን የመሰብሰብ አቅም አለው።

በተጨማሪም የመረጃ መቀበያ ጣቢያው 24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጥ ነው ሲሉ ገልጸው፤ ይህም ሀብትን በአግባቡ መጠቀም እና የመረጃ መቀበያ ጣቢያ መሠረተ ልማት የኢንቨስትመንት ትርፍን ከፍ ማድረግ ያስችላል ብለዋል።

## በግማሽ ዓመቱ በአንድ ሺህ 220 በካይ ተቋማት ላይ ርምጃ ተወሰዷል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በግማሽ ዓመቱ አንድ ሺህ 220 በካይ ተቋማት ላይ ርምጃ መውሰዱን የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ።

ባለስልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያደረጋቸው ስምምነቶች ያሉበትን ደረጃ ለመፈተሽና የተቋሙን የስድስት ወር አፈጻጸም ለመገምገም ያለመ መድረክ አካሂዷል፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዲዳ ድሪባ እንደተናገሩት፤ የከተማዋን ውበት ለማስጠበቅና የአየር ንብረት ብክለትን የሚያስከትሉ ጉዳዮችን ለማስወገድ በትኩረት እየተሠራ ሲሆን፤ በግማሽ ዓመቱ ከአንድ ሺህ 220 በላይ በካይ ተቋማት ላይ ርምጃ ተወስዷል፡፡

ርምጃው ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤ በማሸግና የገንዘብ መቀጮ በመወሰን የተወሰደ ሲሆን፤ በዚህም የጭፈራና ሆቴል ቤቶች እንዲሁም ፋብሪካዎችና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ችግሩን እንዲቀርፉ በጋራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የሚታሸጉ ተቋማትም በሚሰጣቸው የጊዜ ገደብ ችግሩን የማያስተካክሉ ከሆነ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የንግድ ፍቃድ እስከ ማገድ ደረጃ ይደርሳል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ተቋማቱ የሚያስተዳድሯቸው ሠራተኞች በመኖራቸውና ለሕዝብም አገልግሎት የሚሰጡ በመሆኑ ሕግና ደንብን ተከትለው ሊሠሩ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የጭፈራ ቤቶችና ሆቴሎች በመኖሪያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎችና ሌሎች መሰል አካባቢዎች ላይ እንዲሠሩ ፍቃድ በሚሰጥበት ወቅት ችግሮች እየተፈጠሩ በመሆኑ ከከተማው ንግድ ቢሮ ጋር በመሆን የማስተካከል ጥረቶች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡

በዓመቱ 10 ሺህ አገልግሎት ሰጪና አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለመቆጣጠር ታቅዶ በስድስት ወራት ውስጥ 5 ሺህ በሚጠጉት ላይ ክትትል በማድረግ መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮችን እንዲያስተካክሉ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም 942 የድምጽ ሁከት ይወገድልኝ የሚሉ ግለሰቦች አቤቱታ አቅርበው ምላሽ ለመስጠት ጥረት ተደርጓልም ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ዲዳ ገለጻ፤ በምሽት የሚፈጠሩትን የድምጽ ብክለቶች ለማስወገድ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ሲሆን፤ በቀን የሚሰማውን ብዛት ያለው የድምጽ ሁከት ለመቅርፍ ለሃይማኖት አባቶች፣ ለትምህርት ቤቶችና ለሌሎች የድምጽ ሁከት ለሚያስከትሉና ሊረብሹ ለሚችሉ የማህበረሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡



ፎቶ፡ ሀዲስ አብርሃ

አቶ ዲዳ ድሪባ

አክለውም በሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ኤምባሲዎች፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶችና በሌሎች ስፍራዎች ላይ ትላልቅ ተሽከርካሪዎች የድምጽ ብክለት እያስከተሉ በመሆኑ ችግሩን ለመከላከል ከትራፊክ ፖሊሲና ማኔጅመንት ጋር እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

በመንፈቅ ዓመቱ ከ27 ተቋማት ጋር ስምምነት በመፍጠር በጋራ ለመሥራት ታቅዶ ከ20 ተቋማት ጋር እየተሠራ እንደሆነም ጠቁመዋል።

አያይዘውም ከእያንዳንዱ ቤት፣ ከኢንዱስትሪዎችና ከተሽከርካሪዎች የሚወጡ ጭሶች ተደምረው የከተማውን አየር የሚበክሉ በመሆናቸው እርምጃ የመውሰድ ተግባሩ የሚቀጥል ነው፤ ዜጎችም በድምጽ ያለመረበሽ መብታቸውን ለማስከበር ከባለስልጣኑ ጋር አብረው እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

እንደ አቶ ዲዳ ገለፃ፤ ከተማዋ ያሏትን የተፈጥሮ ፀጋዎች ተጠቅማ ከአፍሪካ ሳቢና ተስማሚ ከተማ እንድትሆን እየተሠራ ነው፡፡ እንዲሁም ዜጎች ከበካይ ድምጾች፣ ከአካባቢ ጽዳት ማነስና ከተያያዥ ችግሮች በመራቅ በተረጋጋ ሁኔታ ህይወታቸውን እንዲመሩ ጥረት እየተደረገ ነው።

የውይይቱ ተሳታፊ ባለድርሻ አካላት በበኩላቸው፤ በባለስልጣኑ እየተከናወኑ ያሉ ጅምር ሥራዎች የሚበረታቱ መሆናቸውን ተናግረው፤ ከተቋሙ ጋር በጋራ ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

## በኦሮሚያ በግማሽ ዓመት ከ57 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰበሰበ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ በ2016 ዓ.ም ግማሽ ዓመት ከ57 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን የኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ፡፡

በክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ መስከረም ደበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በ2016 በጀት ግማሽ ዓመት ከ57 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

እንደ ወይዘሮ መስከረም ገለጻ፤ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከመደበኛ፣ ከማዘጋጃ ቤትና ከውስጥ ገቢዎች 144 ቢሊዮን ብር ለማስገባት ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡

በስድስት ወራቱ 70 ነጥብ 712 ቢሊዮን ብር ለማስገባት ታቅዶ 57 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል ያሉት ወይዘሮ መስከረም፤ በአፈጻጸሙ የእቅዱን 81 በመቶ ማሳካት ተችሏል ብለዋል፡፡

ገቢው ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ15 ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ብልጫ ማሳየቱን አመላክተዋል፡፡

በክልሉ ከሚገኙት 517 ሺህ ግብር ከፋዮች ውስጥ 87 በመቶ የደረጃ "ሐ" መሆናቸውን የገለጹት ኃላፊዋ፤ የተቀሩት 13 በመቶ የደረጃ "ሀ" እና "ለ"መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

የታክስ አሰባሰብ ሥርዓቱን ከታክስ ውሳኔ አሰጣጥ ጀምሮ ዲጂታላይዝ ማድረግ መቻሉን ገልጸው፤ በተያዘው ዓመት ለግብር ከፋዮች በቴሌ ብርና ኢ ብር አማካኝነት የግብር ውሳኔ የማሳወቅና የመሰብሰብ ሥራ መሠራቱን አስረድተዋል፡፡

የክልሉ የስድስት ወራት የግብር ክፍያዎች በቴሌ ብር የተሰበሰበ መሆኑን የገለጹት ወይዘሮ መስከረም፤ የግብር ውሳኔ አሰጣጥ ርቀት ባላቸው ወረዳዎች ላይ በቀደመው አሰራር የቀጠለ ሲሆን፤ ግብር ከፋዮች ቴሌ ብርን የመጠቀም ሁኔታቸው ከፍ እንዲል መደረጉን ተናግረዋል።



ወይዘሮ መስከረም ደበበ

በቀጣይ ዓመት የግብር ውሳኔንና ክፍያ በቴሌ ብርና በሲስተም በመታገዝ የሚሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ አሠራሩ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ቀልጣፋ በማድረግ የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ ችግር ለማሻሻል የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከግብር ከፋዮች በኩል ግብርን በወቅቱ ማሳወቅና መክፈል እንደሚጠበቅ ጠቁመው፤ በንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ደረሰኝ የመስጠትና መቀበል እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻም ክልሉ የታክስ ሕግን ማስከበርና የግንዛቤ ማስጨበጫን በመተግበር ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይ የኦዲት ሥራዎችን ማጠናከር፣ የታክስ ሕግ የማስከበር ሥራ በመሥራት የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ እንደሚሠራም አመላክተዋል፡፡

ዜና

# የኅብረት ሥራ ማህበራትን አቅም በማሳደግ የዋጋ ንረትን ማረጋጋት ይገባል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የኅብረት ሥራ ማህበራትን አቅም በማሳደግ የዋጋ ንረትን ማረጋጋት እንደሚገባ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

"የኅብረት ሥራ ማህበራት ሚና ከገበያ በላይ" በሚል መሪ ሃሳብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ10ኛ፤ በአዲስ አበባ ከተማ ለሶስተኛ ጊዜ የሚካሄደው የኅብረት ሥራ ማህበራት ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ሲንፖዚየም ትናንት በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ተከፍቷል።

በመርሀ ግብሩ ላይ የተገኙት የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) እንዳመለከቱት፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዘርፉን በሚጠበቀው ልክ በማሳደግ በየጊዜው እየተባባሰ የመጣውን የምርትና የሸቀጦች ዋጋ ንረት ማረጋጋት ይቻላል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አዎንታዊ ሚና እየተጫወቱ መሆኑን ገልጸው፤ ኤግዚቢሽንና ባዛሩ የተረጋጋ የግብርና ምርቶች ግብይት ሥርዓትን ለማጠናከርና የአምራች ሸማች የጋራ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ተናግረዋል።

የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገትና የዘርፉን ልማት ሁሉን አሳታፊ እንዲሆን በማስቻል ረገድ የኅብረት ሥራ ማህበራት የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአምራቹም ለሸማቹም ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ለከተማዋ ነዋሪዎች የጀርባ አጥንት ሆነው እያገለገሉ ይገኛል።

ከንቲባዋ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ የምርት እጥረት ችግርን በመቀነስ የግብርና ግብዓቶችን በጥራት በማቅረብና ሌሎችም ሚናዎችን በመወጣት ላይ



ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) እና ከንቲባ አዳነች አቤቤ ኤግዚቢሽንና ባዛሩን መርቀው ከፍተዋል

መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የዜጎችን የኑሮ ጫና ለማቃለል እየሰሩ በመሆኑ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ከንቲባዋ አመልክተዋል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የተቋቋሙለትን አላማ ከማሳካት አንፃር ክፍተት አለባቸው ያሉት ከንቲባዋ፤ ችግሩን ለመፍታት የሪፎርም ሥራ በመሥራት የወቅቱን ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙበትን ዕድል መፍጠር ይገባል ብለዋል።

መሰል ኤግዚቢሽኖችም የገበያ ትስስርን ለማሳደግ ዕድል የሚፈጥሩ መሆናቸውን ተናግረው፤ የኅብረት ሥራ ማህበራቱን በመደገፍ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ የሚሰሩ ተግባራት ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም ጠቅሰዋል፡፡

በኢትዮጵያ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኮሚሽንና በአዲስ አበባ የኅብረት ሥራ ማህበራት በጋራ የተዘጋጀው ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ሲምፖዚየም እስከ የካቲት አምስት ቀን 2016 ዓ.ም ክፍት ሆኖ የሚቆይ ሲሆን ከ100 ሺህ በላይ ሰዎች ይጎበኙታል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተገልጿል።

# የአየር ንብረት ለውጥ የሚፈጥረውን ተግዳሮት ለመከላከል በትብብር መሥራት ያስፈልጋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የአየር ንብረት ለውጥና የአካባቢ መራቆት አርብቶ አደሮች ላይ የሚፈጥረውን ተግዳሮት ለመከላከል በትብብር መሥራት እንደሚያስፈልግ የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ፍቅሩ ረጋሳ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡ የአርብቶ አደሮችን ችግር የሚያቃልል ፕሮጀክት ይፋ ሆነ፡፡

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታው ፕሮጀክቱ ይፋ ሲደረግ እንደተናገሩት፤ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሮች 15 በመቶ የሚሆነውን የእንስሳት ሀብት ለሀገር ያበረክታሉ፡፡

አርብቶ አደሮች ለሀገራዊ አጠቃላይ ምርትና ለወጪ ንግድ ጉልህ ሚና ቢኖራቸውም በየጊዜው በሚከሰተው ድርቅ እየተፈተኑ መሆኑን ጠቁመው፤ በአየር ንብረት ለውጥና በአካባቢ መራቆት ምክንያት የሚደርስባቸውን ጫና ለማቃለል ተቋማት በትብብር መሥራት እንዳለባቸው አመላክተዋል።

ይፋ የተደረገው ፕሮጀክት የአርብቶ አደሮችን ሕይወት ለመለወጥ ለሚሠሩ ፈጠራዎችና የጋራ ጥረቶች በር ከፋች ሆኖ የሚያገለግል ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በተለይ ከእንስሳት መኖና ውሃ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የነበረውን የመረጃ እጥረት በመቅረፍ የቀድሞ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን ተግባራዊ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

በፕሮጀክቱ መሰረት ተግባራዊ የተደረገው ሥርዓት



ፎቶ፡ ሀዲስ አብርሃ

ፍቅሩ ረጋሳ (ዶ/ር)

የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ የሚቀርብለትን መረጃ መሠረት በማድረግ ተግባራዊ ርምጃዎችን እንዲወስድ ያስችላል ሲሉ አስረድተዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአርብቶ አደሮችን ሕይወት ለማሻሻል የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን አስታውሰው፤ ፕሮጀክቱም ሥራዎቹን ለማሳደግ ትልቅ አቅም የሚፈጥር መሆኑን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ ወደ ትግበራ እንዲገባ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ባለድርሻ አካላት ምስጋና አቅርበው፤ ለስኬታማነቱ ተገቢውን ክትትል ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የአርብቶ አደር አካባቢው የሀገሪቱ አብዛኛው የእንስሳት ሀብት የሚመረትበት መሆኑን ገልጸው፤ በየጊዜው በሚከሰተው ድርቅ ምክንያት በርካታ እንስሳት ጉዳት እንደሚደርስባቸው አመላክተዋል።

የዚህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማም ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ሊኖር የሚችሉ አጠቃላይ ሁኔታዎችን አስቀድሞ በመተንበይ ጉዳቱን ለማስቀረት አልያም ለመቀነስ የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡ ይህም የማህበረሰቡን ሕይወት በማሻሻልና የምግብ ደህንነትን በማረጋገጥ በኩል ጉልህ ሚና እንደሚጫወት ገልጸዋል።

ለፕሮጀክቱ ትግበራ የሚያግዙ መረጃዎች የሚሰራጩት በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች መሆኑን ጠቁመው፤ አሁን ላይ ፕሮጀክቱ ቦረና አካባቢ ትግበራ ላይ እንደሚገኝና በቀጣይነትም ወደ አፋርና ሶማሌ ክልሎች እንደሚስፋፋ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ በግብርና ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ አሊያንስ ፎር ባዮዳይቨርሲቲ በተባለ ድርጅትና ሌሎችም ባለድርሻዎች ትብብር የሚተገበር መሆኑ ተመላክቷል፡፡

# በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከበጋ ስንዴ ልማት ሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

## - በዞኑ ምንም አይነት የፀጥታ ስጋት የለም

**ጌትነት ምሕረቴ**

ሐረር፡- ዘንድሮ በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን 93 ሺህ ሄክታር መሬት በበጋ ስንዴ መሸፈኑንና ከእዚህም ሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ የዞኑ አስተዳደር ገለጸ፡፡

የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ምክትል ዋና አስተዳዳሪ አቶ አያሌው ታከለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአሁኑ ጊዜ በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ብዙ የልማት ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል አንዱና ዋነኛው ግብርና ነው። በተለይ ዘንድሮ በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን 93 ሺህ ሄክታር መሬት በበጋ ስንዴ መሸፈኑንና ከዚህም ሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

በዞኑ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የበጋ ስንዴ የማልማት ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ አውስተው፤ በ2013 ዓ.ም በስድስት ሺህ ሄክታር መሬት በበጋ ስንዴ መሸፈኑን ለአብነት አንስተዋል፡፡

በበጋ ስንዴ ልማቱን በ2014 ዓ.ም ደግሞ ወደ 14 ሺህ ሄክታር መሬት ማሳደግ መቻሉን ገልጸው፤ የበጋ ስንዴ ምርታማነትም በየዓመቱ እየጨመረ መምጣቱን ተናግረዋል። ለአብነትም በ2013 ዓ.ም በአማካይ በሄክታር 17 ኩንታል የስንዴ ምርት መገኘቱንና ዓምና በአማካይ በሄክታር 58 ኩንታል ምርት መገኘቱን ገልጸዋል።

ዘንድሮ ደግሞ በአማካይ በሄክታር 85 ኩንታል ይገኛል ተብሎ ታቅዶ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አያሌው፤ የበጋ ስንዴ ምርታማነት በየዓመቱ ምርታማነቱ እየጨመረ እንደመጣ በተግባር አይተናል ብለዋል።

ቀደም ሲል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ይቸገር እንደነበር አውስተው፤ ባለፉት አራት ዓመታት በተሠሩት የግብርና ሥራዎች ከተረጂነት ወጥቶ የዞኑ የምግብ ዋስትናውን አረጋግጧል። ለውጭ ገበያ በሚቀርበው ስንዴም የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ እንደሚገኝ አስገንዝበዋል።

በዞኑ በአረንጓዴ አሻራም ብዙ ሥራዎች መሠራታቸውን ምክትል አስተዳዳሪው አያይዘው ገልጸዋል፡፡

ቀደም ሲል የምሥራቅ ሐረርጌ ተራራዎች የተራቆቱ እንደነበሩ ጠቅሰው፤ በተከታታይ ዓመታት በዞኑ በተሠራው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በርካታ ችግኞች ተተክለዋል ብለዋል።

ለአብነትም ባለፈው ክረምት ወቅት 45 ሚሊዮን ችግኝ መተከል መቻሉን አንስተው፤ ይህ የአረጓዴ አሻራም ወጣቶች ንብ በማነብ፣ ከብቶችን በማድለብ፣ ዶሮ ዕርባታና በመሰል የግብርና መስኮች የሥራ ዕድል መፍጠሩን ተናግረዋል። ለአርሶ አደሩም ምርት ምርታማነት እንዲጨምር አድርጓል ።

ሰላምና ጸጥታን በተመለከተ በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ሰላምና ጸጥታን ለማረጋገጥ ብዙ ሥራዎች መሠራታቸውን አቶ አያሌው አመልክተዋል።

ወጣቶች፣ አባገዳዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የጸጥታ ኃይሉ በቅንጅት በሠሩት ሥራም በዞኑ በሚገኙ 23 ወረዳዎችና 583 ቀበሌዎች ምንም አይነት የጸጥታ ስጋት የለም ብለዋል።

በተፈጠረው አስተማማኝ ሰላምም ሕዝቡ፣ ነጋዴውና ኢንቨስተሩ በማንኛውም ቦታና ጊዜ ተንቀሳቅሰው እየሠሩ ይገኛሉ። ይህ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ገልጸዋል።

በዚህም የዞኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ቀን ከሌሊት ያለአዳች ስጋት እየተከናወኑ ነው ብለዋል።

በአሁኑ ጊዜም በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ማንኛውም ሰው ያለምንም ስጋት ተዘዋውሮ መስራትና መኖር ይቻላል ሲሉ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለትውልድ የሚተላለፍ ተምሳሌታዊ ጽናት!

ሀገራዊ ለውጥ የተሻለ ነገር ለመፍጠር የሚደረግ ማኅበረሰባዊ ክስተት ነው፤ በአግባቡ መመራት ካልተቻለ ይዞት ሊመጣው የሚችለው አደጋ /ምስቅልቅል ከፍያለ ነው። ለዚህም ደግሞ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ነጋሪ የሚያስፈልገን አይደለም። እንደ ሀገር በተለያዩ ወቅቶች ሞክረናቸው ያልተሳኩ ለውጦች እንደሀገር ያስከፈሉን ዋጋ ምን እንደሚመስል ለሁላችንም የተሰወረ አይደለም።

አብዛኞቹ ፣ በተለይም በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የተካሄዱ የለውጥ ታሪኮቻችን በለውጥ ፈላጊው ኃይል መካከል ሳይቀር መግባባት / መደማመጥ ሳይቻል ቀርቶ ተስፋ የተጣለባቸውን ያህል ውጤታማ ሳይሆኑ ቀርተዋል። በብዙ ተቃርኖዎች ተፈትነው መሻገር የሚያስችል አቅም በማጣታቸው ሀገርና ሕዝብን ብዙ ዋጋ እንዲከፍሉ አድርገውታል።

ከዚህም ባለፈ ለውጥ በባህሪው ፤ የተሻለ አስተሳሰብ የሚወልደው፤ተሸክሞ የሚያሻግረው መሆኑ፤ ይህም ተጨባጭ በሆነው ሀገራዊ የፖለቲካ ንቅናቄ ባለመታገዙ፤ ዛሬም ትውልዶች የሚፈልጓቸው የለውጥ አስተሳሰቦች ተግባራዊ እንዳይሆኑ ተግዳሮት ሆነዋል። ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉም አድርጓቸዋል።

በኃይል እና ኃይል በሚፈጥረው የአሸናፊ፣ ተሸናፊ ትርክት ላይ መሰረቱን አድርጎ ዘመናት ያስቆጠረው የሀገሪቱ የፖለቲካ ባህል ፤ የሕዝባችንን የለውጥ መሻት፤ትርጉም ያለው ፍሬ እንዳያፈራ በማድረግ ፤በየዘመኑ ትውልዶች ከተስፋዎቻቸው ጋር የሚጋጩበትን ሰፊ የታሪክ ገጽ ፈጥሯል።

ይህ ታሪካዊ እውነታ በባለፉት አምስት የለውጥ ዓመታት ላይም ጥላ እንዳጠላ የሚዘነጋ አይደለም። መላው ሕዝባችን በብዙ ተስፋ እና መስዋእትነት የጀመረው ለውጥ በብዙ የውስጥና የውጪ ፈተናዎች ውስጥ ለማለፍ ተገድዷል። በዚህም ሕዝቡና የለውጥ ኃይሉ ብዙ ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ ሆኗል።

በርግጥ በብዙ ተቃርኖዎች የሚታጀቡ የለውጥ ምዕራፎች ለስኬታማ ፍጻሜያቸው ከሁሉም በላይ የለውጥ ኃይሉን አቅም የሚጠይቁ ናቸው። የለውጡን ዘላቂ ስኬት ማየት፤ ተገማችና ተገማች ያልሆኑ ችግሮችን ተገንዝቦ መፍታት የሚያስችል ፤በለውጥ ኃይል ማንነት የሚለካ የስብእና ዝግጁነት የሚጠይቅ ነው።

ከስልጣን /ከመቀመጫ ባለፈ ለውጥ አማጭ የሆኑ ሀገራዊ ስብራቶችን አውቆና ተረድቶ ማከም ፤ለውጥ በራሱ የአዲስ ታሪክ ምዕራፍ ጅማሬ መሆኑን ተገንዝቦ የራስን የታሪክ ገጽ በደመቀ ቀለም ጽፎ ትውልዳዊ ኃላፊነትን የመወጣት የውስጥ መሻት ፤ለዚህ የሚሆን የማይሰበር ጠንካራ ማንነት የሚፈልግ ነው።

በጅማሬ ውስጥ ፍጻሜን አሻግሮ ማየት የሚያስችል ፤ በእያንዳንዱ የዕለት ተዕለት የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የራስን ታሪክ ሠሪነት እያጸኑ ፤ በሚሠራ ታሪክ ፤ታሪክ ሠሪ ማንነት ያለው ትውልድ እየፈጠሩ ፤ የሀገር እና የሕዝብን የተሻሉ ነገዎች በጠንካራ መሠረት ላይ ማዋቀርን የሚጠይቅ ነው።

ታሪክ በመሥራት እና ታሪክ የሚሠራ ትውልድ በመፍጠር ከሚገኝ ደስታ ዛሬዎችን የበለጠ ትርጉም እንዲኖራቸው ማድረግ ፤ ለዚህ የሚሆን የተከፈተ ልብ፣ አዕምሮና ዓይን ባለቤት መሆን፤ ለውጥን ከሚመራ ኃይል የሚጠበቅ ነው። የለውጡ ቀጣይነትም ማስተማመኛም ይኸው ነው።

ባለፉት አምስት የለውጥ ዓመታትም ለውጡ ያስገኛቸው ተስፋዎች ፤ብዙ የለውጥ ኃይሎችን መፍጠርና በጽናት ማስቆም አስችለዋል። እጅግ ብዛት ያላቸው የለውጥ ኃይሎች ፤ መራራ በሆነ የለውጥ ተሞክሮዎች ውስጥ ለማለፍ ቢገደዱም በለውጡ በነበራቸው የጸና እምነት በጥንካሬያቸው በመዝለቅ ከፈተናዎች በላይ መሆናቸውን በተጨባጭ ማሳየት ችለዋል።

ሀገርና ሕዝብ አስቸጋሪ በሚባል የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ በተገኙባቸው ወቅቶች ፤ለውጡ ይዟቸው በመጣቸው ተስፋዎች አቅም እየገዙ፤ፈተናዎቹ የሚጠይቋቸው መስዋዕትነቶችን ሳያቅማሙ በመክፈል ፤ ሀገርና ሕዝብን ፈተናዎቹ ከፈጠሯቸው ክፉ ቀናት ማሻገር ችለዋል።

ከዚህ አንጻር ትናንት ከፍ ላለ ኃላፊነት ታጭተው ፤ወደ ስልጣን የመጡ የለውጥ ኃይል አባላት ፤ አሁንም እንደ ትናንቱ ለውጡ በደረሰበት ምዕራፍ ለሚጠይቀው መስዋዕትነት ራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።አዲሱ የለውጥ መንገድ ይዞት ከመጣው አዲስ የፖለቲካ እሳቤ አኳያ ለስኬታማነቱ የሚፈልገውን አርቆ አሳቢነት ፤ትዕግስትና ሆደ ሰፊነት ዋነኛ የትግል ስትራቴጂ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በክብር የተሰናበቱ የለውጥ ኃይሉ አባላትም ፤በለውጡ ውስጥ ያላቸው የደመቀ ታሪክ ፤ ለውጡ ይዞት ከመጣው አዲስ ሀገራዊ ትርክት አኳያ ፤ በአሁኑም ሆነ በመጪው ትውልድ ልብ ውስጥ የሚኖረው ስፍራ የከበረ ነው። ፈተናዎችን የተሻገሩበት ጽናትም፤ ተምሳሌታዊነቱ ትውልድ ተሻጋሪ ነው!

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et
**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሃይማኖት የችግር መፍቻ እንጂ ምንጭ እንዳልሆነ አስተምሮዎቻችን በተጨባጭ ሊያሳዩን ይገባል

ቃለአብ ኢያሱ

ሃይማኖትና ምግባር ተጣጥመው መሄድ ያለባቸው የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው የሚባለው ሃይማኖተኞች የሃይማኖታቸውን አስተምህሮ በሥራ የመተርጎም የውዴታ ግዴታ እንዳለባቸው ስለሚታመን ነው። ከዚህ አንጻር በተለይም የሃይማኖት አባቶች ለምዕመናን የሚሰብኩትን እና የሚያስተምሩትን ኖረው በማሳየት ግንባር ቀደም ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ከዘጠና አምስት በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖተኛ እንደሆነ ይነገራል። የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ ከፈጣሪው ጋር ተቆራኝቶ መኖርን የሚመርጠው ወይም በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ የሚታቀፈው በምድር ላይ ሲኖር ጸጋ እና በረከትን ፤ ሲሞት ጽድቅን አገኛለሁ ብሎ በማሰብ ነው።

ሃይማኖቶች በዋና ዋና አስተምህሮዎቻቸው ቢለያዩም በርካታ የጋራ እሴቶች አሏቸው። ፍቅርን፣ ሰላምን፣ እርቅን፣ መተዛዘንን፣ ኅብረትን፣ አንድነትን ይሰብካሉ። አትግደል፣ አትስረቅ፣ አታመንዝር ፣ እናትና አባትህን አክብር፣ በሀሰት አትመስክር፣ ባለንጀራህን እንደራስህ ወደድ ... የሚሉት በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው።

**ከሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ወጣ ብለን ስንመለከት ደግሞ የሰው ልጅ በተፈጥሮም የተሰጡት ሰብዓዊ ባህሪዎች አሉት። ከእነዚህም እንደ መራራት ፣ ማዘን ፣ መሳቅ፣ ማስተዋል፣ ማመዛዘን የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል**

ከሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ወጣ ብለን ስንመለከት ደግሞ የሰው ልጅ በተፈጥሮም የተሰጡት ሰብዓዊ ባህሪዎች አሉት። ከእነዚህም እንደ መራራት ፣ ማዘን ፣ መሳቅ፣ ማስተዋል፣ ማመዛዘን የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። ሰው ሃይማኖት ይኑረውም አይኑረውም መልካም ነገርን እንዲያስብና እንዲሠራ የሚያደርጉት እነዚህ የተሰጡት ተፈጥሯዊ ጸጋዎቹ ናቸው።

ሰው ጥሩ ሥራ ሲሠራ ህሊናው ይረካል፤ መጥፎ ሥራ ሲሠራ ደግሞ የገዛ ሕሊናው ይወቅሰዋል። መልካምነት የህሊና ምግብ በመሆኑ ሰው ሁሌም ለራሱ ሲል የሚተገብረው ጉዳይ ነው፡፡እነዚህ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶቻችን ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ለዘመናት ሰምና ወርቅ ሆነው እንዲኖሩ ያስቻሉ ሀብቶቻችን ናቸው።

ከሰማንያ በላይ ብሔር ብሔረሰቦች እና ከመቶ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕዝቦች ማህበራዊ ትስስራቸውን አጠናክረው በሀገራቸው ጉዳይ እንደ አንድ ሰው እያሰቡ እዚህ ድረስ እንዲዘልቁም አድርገዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖተኛ እና ፈጣሪውን የሚፈራ ነው ሲባል እንደው ዝም ብሎ ያገኘው ሳይሆን በሃይማኖት አባቶች ትጋትና ብርታት ነው። ለዚህም የሃይማኖት አባቶችን ማመስገን ያስፈልጋል።

ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ ችግር ሲገጥማትና ማህበራዊ ቀውሶች ሲፈጠሩ ሕዝቦቿ አንድ ላይ ቆመው ችግሮችን የማስወገድ ልምድ ያላቸው ናቸው። የሃይማኖት አባቶችም ቢሆኑ ሕዝቦችን በማረጋጋት፣ በማስታረቅ፣ በመጸለይ፣ በማጽናናትና አይዟችሁ በማለት ከጥንት ጀምሮ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ቆይተዋል ።

አሁን አሁን ግን ከዚህ ያፈነገጡ ተግባራትን በአደባባይ ማየትና መስማት እየተለመደ መጥቷል። ሀገርን ከገባችበት የሰላም ችግር ለመታደግ ሰፊ ሥራዎች እየተሰሩ ባለበት ሁኔታ ፤ ከሃይማኖታዊ አስተምሮዎቻችን ወጣ ያሉ ሕዝብን ለግጭት የሚገፋፉ የሃይማኖት አባቶችንና ሃይማኖተኞችን እያስተዋልን ነው።

የሃይማኖትን ጭምብል ለብሰው ዘረኝነትን የሚሰብኩና የራሳቸውን የፖለቲካ አቋም የሚያራምዱ፤ ተሰሚነታቸውን ተጠቅመው ጠብ አጫሪ፣ ቀስቃሽና አፍራሽ መልዕክቶችን የሚያስተላልፉ፤ እነርሱ ከሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ውጪ መጓዛቸው ሳያንስ ሌሎችም ቀናውን መንገድ ትተው የእነርሱን የጥፋት መንገድ እንዲከተሉ የሚጎተጉቱ የሃይማኖት አባቶችን እያየን ነው።

ሕዝብ እንደጠላት እንዲተያይ፤ አንዱ ሌላውን እንዲያሳድድ፣ እንዲያጠፋ፣ በሕዝቦች መካከል መተማመን እንዳይኖር የሚሠሩ ፣ መንግሥትንና ሕዝብን ለማቃቃር የሚደክሙ ሃማኖተኞችንና የሃይማኖት አባቶችን እዚህም እዚያም እያየን ታዝበናቸዋል፤ አፍረንባቸዋልም።

በእርግጥ ሃይማኖትና ምግባር አብረው ካልሄዱ እንዲህ አይነት አስገራሚና አሳፋሪ ጉዳዮች መፈጠራቸው የማይቀር ነው። በሰላሙ ጊዜ ሲያስተምሩን ‹‹እግዚአብሔር ዘረኝነትን አይወድም፤ ግራህን ሲመቱህ ቀኝህን ስጥ፤ አትግደል ፣ አትራገም፤ በቀል የእግዚአብሔር ነው አትበል፤” እንዳላሉ ሁሉ ትንሽ ኮሽ ሲል በየዘር ከረጢታቸው ውስጥ ገብተው ያን ሁሉ ያስተማሩትን ሃይማኖታዊ ትምህርት በተቃራኒ እንተርጉም የሚሉ ሃይማኖተኞችን አይተን ኩምሽሽ ብለናል። የሃይማኖትን ጭንብል በለበሱ ብሔርተኛ ሃይማኖተኞችና የሃይማኖት አባቶች ምክንያት ኢትዮጵያ የቱን ያህል እየተፈተነች እንደሆነም እያየን ነው።

የበጎች እረኛ የሆኑት የሃይማኖት አባቶች ከሚሰብኩት ሃይማኖታዊ አስተምህሮ አፈንግጠው ከክፋት ተዋናዮች ጎን መሰለፋቸው ሊያስደነግጠን ይችል ይሆናል። ነገር ግን የሃይማኖት አባቶችም ቢሆኑ እንደኛው ሰው ናቸውና አንዳንድ ጊዜ ስሜታዊ ሲሆኑ የአፍ ወለምታ ሊያጋጥማቸው ይችላል። ማለትም የመድረክ ሞቅታን ተከትለው ፈር የለቀቀ ንግግር ሊያደርጉ ይችላሉ ማለቴ ነው፡፡

በዚህ አንኮንናቸውም። ለምን ቢባሉ ለምሳሌ በክርስትና እምነት አስተምህሮ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመረጣቸው አስራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል እንኳ በፈተና የወደቁ ነበሩና ነው። የይሁዳ ፍጹም የሆነ ክህደት ለዚህ ጽሑፍ ጥሩ ምሳሌ ስለማይሆን ለጊዜው እንተወው።

ሐዋርያው ጴጥሮስ በአንድ ሌሊት ኢየሱስ ክርስቶስን ሶስት ጊዜ ክዶት እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስ እንደሚክደው ያውቃል፤ አስቀድሞም ለጴጥሮስ ነግሮታል፤ ነገር ግን እንደሚክደው እያወቀም ቢሆን መርጦታል፤ ጴጥሮስ በዚያ ቅጽበት የፈጸመው ስህተት አጠቃላይ የእርሱን ሰብዕና እና ማንነት የሚገልጽ አለመሆኑን ኢየሱስ ያውቃል። ለዚያም ይመስላል ጴጥሮስ በፈጸመው ስህተት ውሎ ሳያድር ጸጸቱን በእንባ የገለጸው። ያ ስህተቱ እና ጸጸቱ ደግሞ ለቀጣይ ሕይወቱና ሃይማኖታዊ ተልዕኮው አቅም ፈጥሮለታል።

ሰው የክብሩ ወይም የእውቀት ደረጃው ምንም ይሁን ምን ስህተት ሊሠራ የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል። ዋናው ጉዳይ ግን ከስህተት መታረም ነው። ይህ ሲሆን የበጎ ነገር ምሳሌ መሆን ይቻላል። ከትዝብት መዳን እና ተሰሚነትንም ማግኘት ይቻላል። ከዚያ ውጪ ግን በሥራ ወይም በምግባር የማይገልጹትን ሃይማኖትና የሃይማኖት አባትነት ስም ይዞ ሕዝብን ለክፉ ድርጊት ማነሳሳት ኢ-ሃይማኖታዊም ብቻ ሳይሆን ኢ-ሰብዓዊ እና ኢ-ሕገ መንግሥታዊም ጭምር ነው።

ሃማኖተኞች የሚጠበቅብን ስለሀገር ሰላምና ስለህዝብ ደህንነት መጸለይ እንጂ ዘው ብለን በማያገባንና ባልተጠራንበት ፖለቲካ ውስጥ ገብተን ፤የሀገርን ህልውና ስጋት ውስጥ ፤የሕዝቦችን አብሮ የመኖር እሴት አደጋ ውስጥ የሚከት ፤በሕዝብና በመንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት ፈተና ውስጥ የሚከት ተግባር ውስጥ መገኘት አይኖርብንም። ከማይገቡ ንግግሮች መቆጠብ ይጠበቅብናል። ሃይማኖት የችግሮቻችን መፍቻ ቁልፍ እንጂ ምንጭ እንዳልሆነ እና እንደማይሆን አስተምሮዎቻችን በተጨባጭ ሊያሳዩን ይገባል።

# የአምቦ - ወሊሶ መንገድ ግንባታ ከዘጠኝ ዓመት በላይ በመጓተቱ መቸገራቸውን ነዋሪዎች ገለጹ

**-የአካባቢው አመራሮች መንገዱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ብለዋል**

**ውብሸት ሰንደቁ**

ወሊሶ፡- የአምቦ - ወሊሶ አስፋልት መንገድ ግንባታ ከዘጠኝ ዓመት በላይ በመጓተቱ መቸገራቸውን ኢፕድ ያነጋገራቸው የአምቦ እና የወሊሶ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የአምቦ ከተማ ነዋሪ አቶ ረጋሳ ቡልቶ እንደገለጹት፤ የአምቦ - ወሊሶ አስፋልት መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም እስካሁን አልተጠናቀቀም፡፡

የመንገዱ አለመጠናቀቅ በኅብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታን ከመፍጠሩም በላይ የእንቅስቃሴ እክል እንዲፈጠር አድርጓል ብለዋል፡፡

በአካባቢው የተገነባው የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት በሁለት ዓመታት ውስጥ እንደተጠናቀቀ ያነሱት አቶ ረጋሳ፤ መንግሥት ለዚህ የመንገድ ፕሮጀክትም ተመሳሳይ ክትትል እንዲያደርግ ጠይቀዋል፡፡

የወሊሶ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ረታ ወንድሙ በበኩላቸው፤ የአስፋልት መንገድ ፕሮጀክቱ 68 ኪሎ ሜትር ርዝመት እንዳለው ገልጸው፤ በርካታ ዓመታትን ቢያስቆጥርም ሊጠናቀቅ አለመቻሉ እንዳሳዘናቸው ተናግረዋል፡፡ በማኅብረሰቡ ዘንድም ቅሬታ እንደፈጠረ አንስተዋል፡፡

የወሊሶ ከተማ ከንቲባ አቶ ዳኛቸው ተሾመ በሰጡት ምላሽ፤ የአምቦ - ወሊሶ አስፋልት መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት መጓተቱን አምነዋል፡፡

የአምቦ - ወሊሶ አስፋልት መንገድ ፕሮጀክት የተጀመረው በ2006 ዓ.ም መሆኑን የተናገሩት ከንቲባው፤ መንገዱ እስካሁን አለመጠናቀቁን ነው የተናገሩት፡፡

ሆኖም ከአምቦ እስከ ወንጪ ያለው የአስፋልት መንገድ መጠናቀቁን ጠቅሰው፤ ቀሪውን ከወንጪ እስከ ወሊሶ ያለውን መንገድ በፍጥነት ለማጠናቀቅ እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የመንገድ ግንባታ መጓተቱ እንዳለ አምነው፤ ይህም በኅብረተሰቡ ዘንድ ቅሬታ እንደፈጠረ እናውቃለን ያሉት ደግሞ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ቶሎሳ ተፈራ ናቸው፡፡

የአስፋልት መንገድ ግንባታ ፕሮጀክቱ በፌዴራል መንግሥት የተያዘ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ቶሎሳ፤ ፕሮጀክቱ በፍጥነት እንዲጠናቀቅ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አቅጣጫ ተቀምጦ በመከላከያ ሚኒስትር አብርሃም በላይ (ዶ/ር) ተቆጣጣሪነት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ይህም መንገዱ በሀገሪቱ ከፍተኛ አመራሮች ዘንድ ትኩረት እንደተሰጠው ማሳያ መሆኑን ጠቅሰው፤ ፕሮጀክቱ በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅ እየተሠራ ስለመሆኑ አብራርተዋል፡፡

# ኢትዮጵያ ‘የብሪክስ አዲስ የልማት ባንክ‘ን እንድትቀሳቀል አባል ሀገራቱ ድጋፍ እያደረጉ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የብሪክስ አዲስ የልማት ባንክን እንድትቀላቀል አባል ሀገራቱ ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በወቅታዊ የዲፕሎማሲና ግንኙነት ሥራዎች ዙሪያ ለመገናኛ ብዙኃን ሳምንታዊ መግለጫ ሰጥቷል።

መግለጫውን የሰጡት የሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በውጭ ግንኙነትና ባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ ስኬታማ ሥራዎችን እያከናወነች ትገኛለች፡፡

ኢትዮጵያ የብሪክስን አዲስ የልማት ባንክ እንድትቀላቀል አባል ሀገራቱ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ የዓለም የፋይናንስ ሥርዓት ፍትሐዊነት እንደሚጎድለው ተናግረዋል፡፡

ፍትሐዊነት የሚጎለው የፋይናንስ ሥርዓት እንዲስተካከል ድምጽ ማሰማት ተገቢ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያም የአፍሪካውያን ድምጽ ታስተጋባለች፤ የባንኩ አባል ለመሆንም ከአባል ሀገራቱ ጋር በቅርበት እየሠራች ትገኛለች ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ የብሪክስ አባልነት ዓላማው ለኢኮኖሚው ዕድገት ድጋፍና አቅም እንዲኖር ማስቻል ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሥራችን ማዕከልና አንጓ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ከየትኛውም ሀገር ጋር በተናጠል የምናደርገው ግንኙነት የኢኮኖሚ ትብበርን ለማጠናከር ያለመ ነው ብለውም፤ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል ከሆኑ ሀገራት ጋር በተናጥል ያላት ግንኙነት ጥሩ የሚባል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ አምባሳደር መለስ ገለጻ፤ የብሪክስ አባል መሆን የሌላ ጠላት መሆን ማለት አይደለም፡፡ ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ውጪ ሌላ ዓላማም የለውም፡፡ ለየትኛውም ሀገር የዲፕሎማሲ ሥራ መነሻውና መድረሻው ብሔራዊ ጥቅም ነው፡፡

ኢትዮጵያ ሰጥቶ በመቀበል መርህ ከተለያዩ ሀገሮች ጋር በተናጠል እንደምትሠራ የገለጹት አምባሳደሩ፤ እንደ ብሪክስ ካሉ ተቋማት ጋርም በጋር ትሰራለች ብለዋል፡፡

በተናጥል ከሀገሮች ጋር ካለን ግንኙነት ባሻገር እንደ ተቋም ያለንን ግንኙነትና አስተዋጽኦ የበለጠ ማጠናከር ያስፈልጋል ብለዋል፤ ኢትዮጵያ ብሪክስን ስትቀላቀል ለመቀበል ብቻ ሳይሆን ለመስጠት ጭምር በመሆኑ ንቁ ተሳታፊ እንደምትሆን ገልጸዋል፡፡

በተያያዘ ዜና የኢትዮጵያና የሶማሊያ ሕዝቦች አንድና ጠንካራ ግንኙነት አላቸው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ በሶማሊያ ያሉ ኢትዮጵያዊያንን ደህንነት የሚጠበቀው በሶማሊያ ሕዝቦችም ጭምር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ሰሞኑን በደቡባዊ ሶማሊያ ቤሌድ ሀዎ በጌዶ የነበረው ጥቃት የደረሰው በአሸባሪዎች ነው፤ ሁሌም የአሸባሪዎች የጥቃት አላማ ሕዝቦች በመንግሥት ላይ ያላቸውን እምነት መሸርሸር ነው፡፡ በዚህ አካባቢ የደረሰውን ጥቃት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እየተሞከረ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሳምንቱ በርካታ ዲፕሎማሲ ግንኙነቶች የተከናወኑ ሲሆን፤ የኢትዮ ሩሲያ የፖለቲካና ቢዝነስ መድረክ፣ የኮሞሮስ ፕሬዚዳንት የኢትዮጵያ ጉብኝት፣ የኢትዮ-ጅቡቲ 127ኛ ዓመት የዲፕሎማሲ ግንኙነቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እንዲሁም በ37ኛው የአፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ ከአባል ሀገራት በተጨማሪ በጉባዔው የተመድ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ፣ የኢጋድ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ፣ የዓረብ ሊግ መሪዎች እንደሚታደሙ አምባሳደር መለስ ገልጸዋል፡፡

# አቶ ተመስገን ጥሩነህ የኢፌዴሪ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲሁም ዶክተር መሰረት ዳባን የጤና ሚኒስትር በማድረግ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) እጩዎቹን ባቀረቡበት ወቅት፤ ለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት የተሾሙት አቶ ተመስገን ጥሩነህ በቂ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው፣ በወጣትነት ዘመናቸው ሀገራቸውን በውትድርና የሕይወት ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ሆነው ያገለገሉ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በፖለቲካው ጎራ ከተቀላቀሉ በኋላም ከታችኛው እርከን አንስቶ በብዙ ተቋማት በአመራርነት በታማኝነት፣ በትጋት፣ በቅንነት ያገለገሉ፣ በአማራ ክልል ከዞን አመራርነት እስከ ርእሰ መስተዳድርነት እንዲሁም በተለያዩ የፌዴራል ተቋማት የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ማገልገላቸውን አንስተዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴም በዓለም አቀፍ መድረክ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ የተከራከሩ፣ በዘርፉ ታሪክና ጀግንነት የፈጸሙ ለሥራውም የቀረቡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በተለያዩ የውጭ ሀገራት የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው በዲፕሎማሲው መስክ ኢትዮጵያን ያገለገሉ እንዲሁም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሚኒስትር ዴኤታነት ያገለገሉ፣ በዓለም አቀፍ ተቋማትም ልዩ ልዩ ኃላፊነት ላይ የሠሩ መሆናቸውን ነው ያብራሩት፡፡

ልምድና ተሞክሯቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ምንም እንኳን የብልጽግና ፓርቲ አባል ባይሆኑም ሀገር ሊጠቅሙ እንደሚችሉ በማመን እንዲሾሙ ውሳኔ ላይ መደረሱንም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ባቀረቡት ዝርዝር ጠቁመዋል፡፡

ዘርፉን ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ሀገራቸውንና የዓለም አቀፍ ፖለቲካን ጠንቅቀው የሚያውቁ ታማኝና ታታሪ ባለሙያ መሆናቸውንም መስክረዋል፡፡

የጤና ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ዶክተር መቅደስ ዳባ በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ረዳት ፕሮፌሰር በመሆን በመምህርነትና በህክምና ትምህርት በኃላፊነት ያገለገሉ፣ የኢትዮጵያ ጽንስና ማህጸን ማህበርን በፕሬዚዳንትነት የመሩ፤ እንዲሁም የዓለምአቀፍ ሥነ ተዋልዶ ጤና ማዕከል ዋና ዳይሬክተር በመሆን ማገልገላቸው ተጠቁሟል፡፡

በዓለም ጤና ድርጅት በዋናው መስሪያ ቤት በጀኔቫ የምክትል ዳይሬክተሩ ልዩ ረዳትና ከፍተኛ ባለሙያ ሆነው በማገልገል ላይ እንደሚገኙና ባካበቱት ልምድ ዘርፉ የሚፈልገውን አመራርነት ለመስጠት የተሻለ ብቃት እንዳላቸው በማመን እንዲሾሙ መወሰኑን ነው የገለጹት፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፤ መተካካቱ የኢትዮጵያን ጥቅም ባስቀደመ፣ አቅም እና ብቃትን ማዕከል ባደረገ መልኩ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ብቃት ያላቸው በዩኒቨርሲቲ፣ በተፎካካሪ ፓርቲዎች ውስጥ ካሉ የብልጽግና ፓርቲ አባል ባይሆኑም በሚደረገው መተካካት ታሳቢ እንዲደረግ በተደረገው ውይይት ፓርቲው መወሰኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አመልክተዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲ፣ በተፎካካሪ ፓርቲዎች ውስጥ ብቃትና ልምድ ያላቸው ካሉ ወደ ፊት በሚደረጉ ሽግሽጎችም እንዲካተቱ ይደረጋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) በካቢኔው ውስጥ የሌሎች ፓርቲ አመራር የሆኑ አባላት በፊት ከነበረው ልምድ በተለየ ሁኔታ በስፋት መካተታቸውንና ትግበራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አመልክተዋል፡፡

ስልጣን በኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ፣ በንግግር፣ በምክክር ብቻ የሚገኝ እንዲሆን ሁሉም በኃላፊነት መሥራት ይገባዋል ብለዋል፡፡

ምክር ቤቱ ለ32 ዓመታት በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃ ያገለገሉትን አቶ ደመቀ መኮንንም አመስግኖ ከመንግሥት ኃላፊነታቸው በክብር ሸኝቷል ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡

ላለፉት 12 ዓመታት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትን አቶ ደመቀ መኮንን በሚመለከት አሁን የተወሰነው በምክክርና በውይይት መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር)፤ በሰላማዊ መንገድ ስልጣን መረካከብና ኢትዮጵያን ላገለገሉበት ተመስግነው መሄድ ተጨማሪ ክብር ነው ብለዋል፡፡

በውጭ ብዙ አሉባልታና ወሬ ቢሰማም ሁሉም በምክክር፣ በውይይትና በመግባባት የተደረገ ስለመሆኑም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናግረዋል፡፡

በተያያዘ ዜና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አምባሳደር ሬድዋን ሁሴንን የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም ትዕግስት ሃሚድን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አድርገው መሾማቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አስታውቋል፡፡

# ረጂ ተቋማት ርዳታ ካቋረጡ በኋላ መንግሥት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ወደ ስምንት የሚደርሱ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት መጋዘኖች አሉት፡፡ በዚህ አማካኝነት የተደራጁ በርካታ ዩኒየኖች የተለያዩ ድጋፎችን ወደየ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶቹ ገቢ ያደርጋሉ፡፡

ድርቅን ጨምሮ ሌሎችም ጉዳቶች መቼ ሊከሰቱ እንደሚችሉ ስለማይታወቅ በዚህ ሁኔታ የመጠባበቂያ ክምችቱ ሁልጊዜም ዝግጁ እንደሆነ የገለጹት አቶ አታለለ፤ መንግሥት በአንደኛ ዙር ለ7 ነጥብ 3 ሚሊዮን፣ በሁለተኛ ዙር 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን እንዲሁም በሦስተኛ ዙር ለ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ አድርጓል ነው ያሉት፡፡

በሶስተኛው ዙር ድጋፍ መንግሥት ባደረገው የዲፕሎማሲ ሥራም ረጂ ተቋማት መንግሥት መር በሆነ የእርዳታ አሰጣጥ ፖሊሲ አማካኝነት 20 በመቶ ድርሻ እንደነበራቸውም አንስተዋል፡፡

አራተኛ ዙር ድጋፍ ለመስጠት በቂ ዝግጅት እየተደረገ እንዳለ ገልጸው፤ በዚህም በርካታ እህል ወደ መጋዘን እየገባና የቅድሚያ ቅድሚያ የሚያስፈልጋቸው የተረጂዎች ልየታ እየተደረገ እንዳለ ጠቅሰዋል፡፡ በዛሬው ዕለት ከድሬዳዋ የመጠባበቂያ ክምችት መጋዘን ወደ ትግራይ ክልል እንደሚላክም ጠቅሰዋል፡፡

ኮሚሽኑና የፌዴራል መንግሥት ሴክተር መሥሪያ ቤቶች በጋራ በመሆን ዜጎች በምን ዓይነት ሁኔታ እርዳታ ማግኘት እንዳለባቸው ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ “የቤት ለቤት የአኗኗር ዘዴ ልየታ” ጥናት መደረጉን ጠቁመዋል፡ ፡

በዚህም ጥር፣ የካቲትና መጋቢት ወራት ላይ ድርቅና ጎርፍን ጨምሮ የተለያየ ጉዳት ለደረሰባቸው 6 ነጥብ 6 ሚሊዮን ተረጂዎች እንደሚኖሩ ገልጸዋል፡፡ ለነዚህ ዜጎች በቂ የሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጅት መደረጉን ነው ያስታወቁት፡፡ ተደራሽነቱም በቂ በሆነ መንገድ እንደሚከናወን ገልጸዋል፡፡

ክልሎች የቅድሚያ ቅድሚያ የሚያስፈልጋቸውን ዜጎች ለይተው በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ድጋፉ እየተሰጠ እንዳለ ተናግረው፤ በዚህ መሠረት በተለይም በሦስተኛው ዙር ጉዳት የደረሰባቸውን የሰሜኑ ክፍል ዜጎች ላይ ትኩረት ተደርጎ ድጋፉ መሰጠቱን አንስተዋል፡፡

መንግሥት እያንዳንዳቸው እስከ 400 ሺህ ሜትሪክ ቶን እህል መያዝ የሚችሉ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ መጋዘኖች በኩል በቂ ዝግጅት እያደረገ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ በቂ ድጋፍ ማቅረብ የሚችሉ የተደራጁ ዩኒየኖች መኖራቸውን ጠቁመዋል፡፡ በዚህም በየቀኑ እህል ወደ መጋዘኖቹ እየገባ እንዳለም አመላክተዋል፡፡

# “አፊኒ” - የሲዳማ ባሕላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት

በኃይሉ አበራ

ሀገራችን የአያሌ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሙዚየም በመባል ትታወቃለች። እነዚህ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የተለያዩ ባሕሎች ያሏቸው ሲሆን፣ እነዚህ ባሕላዊ እሴቶች በርካታ ፋይዳ አላቸው። ከእነዚህም መካከልም ግጭት ለመፍቻ የሚያገለግሉ ባሕላዊ እሴቶች ይጠቀሳሉ። በሀገሪቱ በርካታ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖራቸው፣ በርካታ ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ እሴቶች እና ባሕላዊ ሥርዓቶች የሚገኙባት እንድትሆን አስችለዋታል።

የእዚህ ግጭት መፍቻ ሥርዓት ባለቤት ከሆኑት መካከልም የሲዳማ ብሔረሰብ አንዱ ነው። ብሔረሰቡ ከጥንት ጀምሮ ሲመራባቸውና ሲተዳደርባቸው የኖረባቸው ለዘመናት ጠብቆ ያቆያቸው ባሕላዊ ተቋማት፣ ዕሴቶች፣ ልማዳዊ አሠራሮችና የእምነት ሥርዓቶች አሉት። ከእነዚህ መካከልም የአስተዳደርና የዳኝነት፣ የግጭት አፈታት፣ ባሕላዊ ሕግና ሥርዓት፣ የሉዋ ተቋም፣ እንዲሁም በኅዘንና በደስታ ጊዜ የሚጠቀምባቸው ባሕላዊ ጨዋታዎች (የአባቶች ቄጠላን ጨምሮ)፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ ባሕላዊ አለባበስና ጌጣጌጦች፣ የዘመን አቆጣጠር ቀመር፣ የቀንና የወራት አቆጣጠርና የዘመን መለወጫ ዕለተ ቀን “ፍቼ” እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ።

መደማመጥ ይበልጥ ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ቁልፍ ሥርዓት እንደሆነ የተመላከተበት እና ለዘመናት ጥቅም ላይ ከዋሉ ባሕላዊ የግጭት አፈታት ሀገር በቀል እሴቶቻችን መካከል በዚህ ጽሑፍ የሲዳማ ብሔረሰብ ባሕላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትን ለማየት ወደናል። በዚህ ባሕላዊ እሴት ላይ በቅርቡ መጽሐፍ የጻፉትን የዶክተር አራርሶ ገረመው ጽሑፍም ለእዚህ ሥራ ተጠቅመናል።

አራርሶ ገረመው (ዶ/ር) በትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ በነገረ መለኮት ከኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂ ኮሌጅ፤ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኮአፐሬቲቭ ዴቨሎፕመንት ከሀዋሳ ዩኒቨርስቲ እንዲሁም የፒኤች ዲግሪያቸውን ከቪዥን ኢንተርናሽናል ከዩ.ኤስ.ኤ ካሊፎርኒያ አግኝተዋል። በአሁኑ ወቅትም በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ሆነው እያገለገሉ ሲሆን፣ ትውልድ በሁለንተናዊ ዕድገት እንዲበለፅግ የሚተጉ እና ከአፊኒ ዲቨሎፕመንት ኢኒሺየቲቭ ፎረም መሥራቾች አንዱም ናቸው።

አራርሶ (ዶ/ር) “አፊኒ” በተሰኘው መጽሐፋቸው እንዳብራሩት ፤“አፊኒ” ወይም በጥሬ ትርጉሙ “ሰማችሁ ወይ?” እየተባለ በሲዳማ ብሔረሰብ ሸንጎ ላይ የሚሠራበት ባሕላዊ ሥርዓት፣ የሸንጎው ታዳሚዎች የሚጠያየቁበት፣ ጥበባዊ ሂደት ያለው አስደማሚ የብሔረሰቡ ባሕላዊ የሠላም እሴት ነው። ይህም የትናንትን የሚያጎላ፣ ለዛሬ ጥንቃቄን የሚያስገነዝብ፣ ለነገ ትኩረት የሚሰጥ የሰጥቶ መቀበልን መርሕ ያዳበረ ዴሞክራሲያዊ የሆነ አካሄድ ያለው ባሕል ነው ሲሉ ያብራራሉ።

በግጭት አፈታት ሂደቱ ላይ የሸንጎው ተሰብሳቢ “ሰማችሁ ወይ?” እየተባባለ የሚጠያየቀው ለጉዳዩ ትኩረት ለመስጠት፣ ልብ ከቀልብ ሆኖ ለመደማመጥ ክርክሩ (ውይይቱ) መስመር እንዳይለቅ እና ከስሜታዊነት ለመጠበቅ እና እውነታውን ለመፈለግ የሚደረግ የግጭት አፈታት ሥርዓት ነው።

በርካታ ጉዳዮች ወደ ግጭት ከሚያመሩባቸው ነገሮች አንዱ አለመደማመጥ እና አንዱ የአንዱን ሀሳብ አለማዳመጥ የሚሉት አራርሶ (ዶ/ር)፣ “የአፊኒ” ሥርዓት አስፈላጊነትም ተገቢውን ጊዜ ወስዶ ነገሩን በአግባቡ ለማብላላትና ለማሰላሰል ይረዳል ሲሉ በመጽሐፉ ላይ አስፍረዋል።

እንደ አራርሶ (ዶ/ር) ማብራሪያ፤ የአፊኒ ሥርዓት ተቋም ነው፤ ጊዜንና ቦታን የያዘ እሴት ነው። አፊኒ በሲዳማ ብሔረሰብ ዘንድ የሚታወቅና የሚከበር ነው፤ ሁሉም ለሥርዓቱ እንዲገዛ የሚያደርግ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ወጉን ጠብቆ አሁንም ድረስ የዘለቀ እሴት ነው። ከ500 ዓመታት በፊት ይኖር የነበረ አንድ የሲዳማ ሰው ምናልባትም ፈጣሪ ፈቅዶ ተመልሶ ቢመጣ ከቴክኖሎጂ ዕድገት አንፃር ሁሉም ነገር ቢቀያየርበት አፊኒን ግን ከነውበቱ እና ግርማ ሞገሱ በሲዳማ ያገኘዋል።

አፊኒ ተቋም ነው ሲባልም በመደበኛ አይነት አሠራር ቢሮ ኖሮት የተቀጠረ ሰው ያለው ተቋም ሳይሆን፣ ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ የሚከወን፣ ነገር ግን አሠራሩ ለሁሉም ግልፅ የሆነ ተቋም በመሆኑ ነው። አፊኒ ቦታ ነው



በሲዳማ ብሔረሰብ ማንኛውም አይነት ግጭት ወይም ችግር በአፊኒ ሥርዓት ሲታይ ይችላል

ሲባልም ሥርዓቱ የሚከናወንበት ቦታና ጊዜው ይሄንኑ ስያሜ ስለያዘ ነው፤ አፊኒ ሥርዓትም፣ ተቋምም እንዲሁም ቦታን አመልካች ነው። አፊኒ የስክነት ውበት፣ የአስተውሎት ጥግ ነገሮችን የመተንተን እና ችግርን በስምምነት እና በጋራ የመፍታት እምቅ አቅም እንዳለው በመጽሐፉ ተጠቁሟል።

የሲዳማ ባሕል ልዩ መገለጫዎች ማለትም ፍቼ-ጫምባላላ (የአዲስ ዓመት በዓል አከባበር)፣ የሉዋ ሥርዓትና በሌሎች በርካታ ባህላዊ እሴቶችና ማኅበራዊ ልምዶች እጅግ የበለጸገ ነው። አፊኒም በሲዳማ ሕዝብ ትልቅ ትርጉምና ቦታ አለው። የአፊኒ ሥርዓት በግጭት አፈታትና ሠላም ግንባታ ሂደት በሲዳማ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚገኝ፣ ታሪካዊና በሰፊው ጥቅም ላይ የዋለ ባሕላዊ ሥርዓት ነው።

የአፊኒ ተቀዳሚ ሚና አስመልክቶ በመጽሐፉ እንደተመለከተው፣ በሲዳማ ባሕል በዋናነት አብሮ መኖር፣ ለጋራ መግባባትና እሴት፣ ለይቅርታና ዕርቅ ምቹ ሁኔታ መፍጠሪያ መድረክ ነው። በተጨማሪም ሰላማዊ፣ ግልጽና ዴሞክራሲያዊ ውይይት በማድረግ ተሳትፎንና ፍትሐዊነትን በከፍተኛ ደረጃ ያጎለብታል። የአፊኒ የመጨረሻ ግብ በሁሉም ጉዳዮች ስምምነት ላይ መድረስ ነው።

የአፊኒ ሥርዓት ልክ እንደ ሲዳማ ብሔረሰብ ታሪክ፣ ብሔራዊ ማንነት፣ ቋንቋና የተለያዩ የባሕል አካላት የረዥም ጊዜ ሁነት መሆኑም በመጽሐፉ ተመልክቷል። ጤናማ ግንኙነትን ለማካሄድና በማኅበረሰቡ መካከል ማንኛውም ውሳኔ ላይ ለመድረስ ልዩ መሣሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ ይውላል። በዚህ ሁኔታ ውይይቱ ወይም ንግግሩ የሚፈለገው ግብ ላይ እስኪደርስ በባሕል መሪዎች ወይም ማኅበራዊ ደረጃቸው ከፍተኛ ቦታና ክብር በሚሰጣቸው አዛውንቶች ይከወናል። ያለ አፊኒ ሥርዓት ምንም ዓይነት ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም።

አራርሶ (ዶ/ር) በመጽሐፋቸው እንዳሉት፤ አፊኒ በሲዳማ ውስጥ እንደ ወሳኝ ያልተጻፈ የሕግ ቻርተር ይቈጠራል። ማንኛውም ግጭት ወይም ችግር በአፊኒ ሥርዓት ሊታይ ይችላል። በማኅበረሰቡ ውስጥ በማንኛውም ደረጃ የሚከሠቱ ከቀላል ጉዳይ ጀምሮ እጅግ ውስብስብ እስከሆኑ ጉዳዮች ድረስ ያሉትን ሁሉንም ጉዳዮች ማስተዳደርም ይችላል።

የአፊኒ ሥርዓት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን ጨምሮ የሴቶችን መብቃት ያበረታታል። ይህም በዋናነት የሴቶችን መሠረታዊ መብቶች ለማስከበርና ለመጠበቅ፤ የወንድ የበላይነትን ለማስወገድ ይጠቅማል። ለምሳሌ “ያካ” በሲዳማ ውስጥ በፆታ ላይ የተመሠረተ ትንኮሳና የሴቶች መብት ጥሰትን ለመቃወምና ለማስጠበቅ በማኅበረሰቡ ዘንድ በሕገ ልቦናነት የታወቀ ጠንካራ ሕግ ነው። የሲዳማ ሴቶች በዚህ ረገድ አፊኒን አስፈላጊ ከሆነ በወንዶች ላይ ከባድና አስተማሪ ቅጣት በመጣል ጉዳዩን ለመቆጣጠር ቁልፍ ሚና የሚጫወትበትን “ያካ” በተደራጀ አግባብ ሠላማዊ ሰልፍ በማድረግ መብታቸውን የሚያስጠብቁበት ስልት አርገው ይጠቀሙበታል።

ሁሉም የአፊኒ ሂደቶች የሚመሩትና የሚተገበሩት በባሕላዊ ደንቦችና ሕጎች “ሴራ” መሠረት ነው። ሴራ ጥፋተኛ ሆነው በተገኙና ከአፊኒ ትእዛዝ ውጪ በሆኑ ግለሰቦች ላይ የሚበየን ከማንኛውም ማኅበራዊ መስተጋብርና ጥቅማ ጥቅሞች የሚያገል፣ ከሌሎች ጋራ የሚኖራቸውን ግንኙነት የሚገድብ የባሕል ማዕቀብ መሆኑን መጽሐፉ ያመለክታል። የሴራ ሥርዓቱና ማዕቀቡ

**የአፊኒ ዕሴት ተነጋግሮ መደማመጥን የተላበሰ፣ ትዕግሥትንና መረጋጋትን የሚያጎናጽፍ፣ መደማመጥን የሚያጎለብት፣ ከመቃቃር ይልቅ ስክነትን የሚመርጥ ትልቅ ሥርዓት ነው**

እጅግ በጣም ከፍተኛና በማኅበረሰቡ አባላት በሙሉ በጥብቅ የሚተገበር እና የተለያዩ ሀገራት በሌሎች ሀገራት ላይ እንደሚጭኑት ዓይነት ማዕቀብ ያህል ከባድ ቅጣት መሆኑንም ያስረዳሉ። አፊኒ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችን በማካፈል፣ እውነታውን (ሐላሌ) በመፈለግና በመመርመር በግጭት አፈታትና በአጠቃላይ ለሠላም ግንባታ ወሳኝ ሂደት መሆኑንም ያስገነዘባሉ።

በአፊኒ ሥርዓት አጥፊ ይቀጣል፤ ተበዳይም ይካሳል። ይህን ሥርዓት የሚጥስና ላለማክበር የሚያንገራግር ግለሰብም ሆነ ቡድን የሚደርስበት ማኅበራዊ ቅጣት ከፍ ያለ ነው። ሴራ በመባል የሚታወቀው ቅጣት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መንፈሳዊ ቅጣት ብቻ ሳይሆን የሚያስከትለው ሥነልቡናዊ ቀውስም በቀላሉ የሚሽር አይደለም።

“አፊኒ” በሸንጎ ውይይት ወቅት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ተሰብሳቢው በነፃነት ሀሳቡን እንዲገልጽ የሚፈቅድ ባሕላዊ ሥርዓት ነው። በመሆኑም በሲዳማ ምድር የሚኖሩ ማናቸውም ብሔረሰቦች በዚህ ሥርዓት መነሻ ትልቅ ዋስትና ይሰማቸዋል። በማኅበረሰቡ መካከል በሚኖሩበትም ጊዜ ከፍተኛ መተማመንና ደህንነትም ይሰማቸዋል። የአፊኒ ዕሴት ተነጋግሮ መደማመጥን የተላበሰ፣ ትዕግሥትንና መረጋጋትን የሚያጎናጽፍ፣ መደማመጥን የሚያጎለብት፣ ከመቃቃር ይልቅ ስክነትን የሚመርጥ ትልቅ ሥርዓት ነው። ይህ ዕሴት የመላ ኢትዮጵያውያንና የአፍሪካውያን የዕርቀ ሰላም ማውረጃ መሣሪያ ቢሆን ምን ያህል ሀገራችንም ሆነ አህጉራችንም ተጠቃሚ በሆነች ሲሉም በቁጭት ይገልፃሉ።

በሲዳማ ባሕል ሰዎች ሲናገሩ “አፊኒ” ሳይባል ጣልቃ አይገባም። በሌላ መልኩ አንድ የተበደለ ሰው ማናቸውንም ዓይነት ርምጃ ከመውሰዱ አስቀድሞ አጠገቡ ላሉት ወይም ለታላላቆቹ “አፊኒ” በማለት ማስታወቅ ባሕላዊ ግዴታው ነው። ይህን ሳያደርግ በግብታዊነት ርምጃ የወሰደ እንደሆነ ባሕላዊ ሴራ (ቅጣት) ይጣልበታል።

“አፊኒ” እውነትን ከማፈላለግና ከፍትሕ አሰጣጥ ጋራ በእጅጉ ይተሳሰራል። እውነትን በማጣራትና በማረጋገጥ ወደሚቀጥለው ተግባር ለመሄድ “አፊኒ” በጉዳዩ ላይ ዕውቀት ያለው ማንኛውም ሰው መረጃ እንዲሰጥ ሰፊ ዕድል ይቸረዋል። በባሕላዊ የአስተዳደርና የዳኝነት ሥርዓት የበለጸገውና የከበረው የሲዳማ ሕዝብ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩትም በላቀ ቁጥር በርካታ ባሕላዊ ዕሴቶችን አክብሮና ጠብቆ በመኖሩ ሊመሰገን ይገባዋል።

በብሔረሰቡ ውስጥ ግጭትና ሁከት እንዳይከሠትም ሆነ ከተከሠተ በኋላ ነገሮችን ለማረጋጋትና ወደ ቀድሞው ሠላማዊ ሁኔታ ለመመለስ የሚደረገው ባሕላዊ ሥርዓት “ሲጮ” በመባል ይታወቃል። ውሳኔ ያገኙ ችግሮች፣ ግጭቶችና ሁከቶች በዕርቅ እንዲያልቁና ዳግመኛ እንዳያገረሹ ቃል ኪዳን የሚገባበት ሥርዓት ደግሞ “ጎንዶሮ” በመባል ይታወቃል።

“ቀጌፌጫ”ም ሌላኛው ባሕላዊ ሥርዓት ነው። ይህም አንድ ሰው ሆነ ብሎ የሌላውን ነፍስ ያጠፋ እንደሆነ በባሕሉ መሠረት የሚወሰንበትን የደም ካሣ ከከፈለ በኋላ በሟችና በገዳይ ቤተሰቦች መካከል የጠላትነት ስሜት እንዳይኖር ለዘለቄታው እልባት የሚበጅበት ሥርዓት መሆኑ በመጽሐፉ ተብራርቷል። ይህም የሚከወነው ሥርዓቱን ማስተዳደርና መምራት በሚችሉ ክፍሎች ነው። ምንም እንኳ የከረረ ጥልና ክርክር ቢኖርም እንኳ በመደማመጥ መርሕ እልባት ሳያገኝ አይታለፍም፤ ለዚህም በየእርከኑ የሚገኙ የሥርዓቱ አስፈጻሚዎች “ሐላሌ”ን ወይም እውነታውን በመፈለግና በመመርመር እንደ መርሕ ይዘው የሚተገብሩት ይሆናል።

ይህ ባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓት የሲዳማ ብሔር በታሪክ ለረዥም ዘመናት ማዕከላዊ መንግሥት ሳይመሠረት የሉዋ ሥርዓት በየጎሣዎቹ ራስ ገዝ የአስተዳደር መዋቅሮችን ዘርግቶ ሲሠራበት ቆይቷል። ሲዳማ ገጸ-ብዙ ባሕሎች፣ ልማዶች፣ ሀገር በቀል ዕውቀቶች እና የአኗኗር ሥርዓቶች ያሉት ብሔር ነው።

አራርሶ (ዶ/ር) የመመረቂያ ጽሑፋቸውን ያደረጉትም በአፊኖ እሴት ነው፤ በአፊኖ ጥበብ፣ በጎንዶሮና በሲጮ ዕሴት ተኮትኩተው ያደጉ የሲዳማ ልጆች በየትኛውም የዓለም ክፍል ውይይት ሲያደርጉ በአፋቸው ቀድሞ የሚመጣው ቃል አፊኒ! እንደሆነ ተናገረዋል። ይህ ሥርዓት ሳይበረዝና በዘመን አመጣሽ ሁኔታ ፈር እንዳይለቅ ትውልዱ በትልቅ አትኩሮት ከአባቶች መማርና ባሕሉንም ከነሙሉ ክብሩ ማስቀጥል አለበት ሲሉም በመጽሐፋቸው አስገንዝበዋል። የሲዳማ ብሔር ሞቴዎች፣ ጋሮዎች ወይም ጌሎዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የተከበሩ የሲዳማ እናቶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ በአጠቃላይ ሕዝቡ ለዚህ ዕሴት መበልጸግ የበኩላቸውን እንዲወጡ ሥልጠናዎችን በመስጠት የበለጠ ሥራ መሥራት አስፈላጊ ነው ሲሉም ያሳስባሉ።

የሲዳማ የሀገር ሽማግሌ “ለወዳጅ ለመወሰን ተሂዶ ለባላንጣ ይፈረዳል” ሲሉ እንደሚናገሩ አራርሶ (ዶ/ር) ጠቅሰው፣ ይህም የእውነትን (ሐላሌ)ን የበላይነት እንደሚያመለክት አስታውቀዋል። ግልጸኛነት፣ ሐቀኝነት፣ ቀጠሮ አሰጣጡ፣ ከነገሩ ጋራ የሚስማማ ተረት እና ምሳሌያዊ አነጋገር አዋዝቶ በማቅረብ ውስብስቡን እንቆቅልሽ የሆነን ችግር እሳት እንደነካው ሰም ይቀልጣል ሲሉም የዕሴቶቹን ችግሮች የመፍታት አቅም ያስረዳሉ። በመጽሐፉ ላይ እንደተመለከተው፤ በአፊኒ እሴት አስታራቂዎቹ የሐላሌ ምትክ ናቸው፤ ሞቴዎች ወይም የጎሣ መሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ማኅበራዊ ጉዳዮችንና ትልልቅ ክሥተቶችን የማስተዳደርና ትክክለኛ መስመር የማስያዝ ሚና በመጫወት ያገለግላሉ። በጎሣ ውስጥ ማኅበራዊ ግጭቶችና አለመግባባቶች ሲከሠቱ ጉልሕ ተሳትፎና ሚናቸውን በማሳረፍ ማኅበረሰቡን የማገልገል ሥራ ይሠራሉ።

የአፊኒ ሥርዓት ማንኛውንም ቅራኔ ግጭቱ ወደ ከፋ ደረጃ ሳይደርስ ለሀገር ሽማግሌዎች በፍጥነት በማድረስና በደል የደረሰበት አካል ሸንጎ በመቅረብ የደረሰበትን ያሳውቃል። በደሉን፣ ኀዘኑን፣ ቅሬታውን በማሳወቅ እነሆ ፍትሕ ስጡኝ የሚል ስሞታውን ያቀርባል። በሸንጎውም የሚሳተፉት የሀገር ሽማግሌዎች፣ ጭሜዬዎች፣ አያንቶዎች፣ የጎሣ መሪዎች፣ ጋዳናዎችና ሌሎችም ለተከሠተው ችግር ብሎም ገና ሊፈጸም ላለው ችግር እጅግ በሳል በሆነ የፍርድ አሰጣጥ የሚዳኙበት እሴት መሆኑንም አራርሶ (ዶ/ር) ያስረዳሉ።

እነዚህን የመሳሰሉ ሀገር በቀል እሴቶችን ልንጠብቃቸው እና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከየትኛውም ጊዜ በላይ አሁን ልንጠቀማቸው ይገባል። እነዚህን እሴቶች ለትውልድ ለማስተላለፍ እንዲሁም በመደበኛው የፍትሕ ሂደት የሚታየውን ጫና ለማቃለል ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን ተገንዝቦ መሥራትም ያስፈልጋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ድሬና ወጣቶቿ

ክብረዓብ በላቸው

በትምህርት፣ በንግድና በተለያየ የሥራ መስክ ተሰማርተው የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ከድካማቸው አረፍ ማለታቸው ተፈጥሯዊ ነው:: በእረፍት ጊዜ ደግሞ አዕምሮንም አካልንም ዘና የሚያደርጉ ነገሮች ያስፈልጋሉ:: በእርግጥ ዘና ስለማለት ሲነሳ ምርጫው ይለያያል::

አንዱን የሚያዝናናው ነገር፤ ሌላው በበጎ የሚያየው ላይሆን ይችላል:: ብቻ ሁሉም የመዝናኛ ምርጫ አለው:: በተለይ ወጣቶች ከትምህርትም ሆነ ከሥራ በኋላ ጊዜያቸውን ባልባሌ ነገር እንዳያጠፉ የተለያዩ የመዝናኛ ማዕከላት ሊስፋፉ እንደሚገባ ብዙዎች ይመክራሉ::

የመዝናኛ ማዕከላት ካልተስፋፉ ወጣቶች በአልባሌ ቦታ ለመዋል ይገደዳሉ፣ ለተለያዩ ሱሶችም ተጋላጭ ይሆናሉ:: ወጣቶችን ማዕከል ያደረጉ መዋያዎች(መዝናኛዎች) ምቹ በማድረግም ከአካባቢ አካባቢም የሚለያይ በመሆኑ የሚሰጡት አስተያየቶችም ከአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ናቸው::

ከሰሞኑ በድሬዳዋ በነበረኝ የሥራ ቆይታ በከተማዋ ያሉትን የመዝናኛ በተለይም ወጣቶች ሊውሉባቸው የሚችሉትን ለመቃኘትና አስተያየትም ለመሰብሰብ ሞክሬ ነበር:: በበቂ ሁኔታ የለም የሚለው አስተያየት ይበዛል:: አንዳንድ ወጣቶችንም አነጋግሬ ተመሳሳይ ነበር ምላሻቸው:: አሁን ላይ ግን ተስፋ የሚሰጡ ጅምር ሥራዎች በከተማዋ እየታዩ መሆኑንም ነግረውኛል::

ከእነዚህ ወጣቶች መካከል ወጣት አበበ ወልዴ አንዱ ነው:: አበበ በድሬዳዋ ገንደ ቦዬ ተብላ በምትጠራ አካባቢ ነው የሚኖረው::

ወጣት አበበ፤ ስለአካባቢው ስያሜም እንደነገረኝ፤ የመኖሪያ አካባቢው ተለውጦ ከተማ ከመሆኑ በፊት ነዋሪዎች አርሶአደሮች ነበሩ:: ገጠር በነበረበት ወቅት በአካባቢው የአሳማ ርቢ ይከናወን ነበር:: በዚህ የተነሳ አካባቢው ገንደ ቦዬ ተባለ:: ቃሉ ኦሮምኛ ነው:: ገንደ፣ መንደር ሲሆን፣ ቦዬ፣ ደግሞ አሳማ ማለት ነው::

ወጣት አበበ፤ ድሬዳዋን ሲገልጻት እንኳን ተወልዶ ላደገባት ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍል ኑሮቸውን በድሬዳዋ ላደረጉም ምቹ እንደሆነች ነው:: ወጣቱ ሊውልባቸው ወይንም ጊዜ ሊያሳልፍባቸው የሚችሉ ምቹ ሁኔታዎች ማሟላት ላይ ግን ከከተማ አስተዳደሩ ብዙ ሥራ ይጠበቃል ይላል:: በዚህ በኩል ለወጣቶች ትኩረት ተነፍጓል ብሎም ያምናል::

ወጣቱ የሙዚቃ፣ የትያትር፣ የሥነጽሑፍ፣ በአጠቃላይ ክህሎቱን ሊያወጣ የሚችልባቸው የተለያዩ ክበባት እንዲሁም ሲኒማ ቤቶች፣ ፓርኮችና ሌሎችም ጊዜ ማሳለፊያዎች ይኖሩ እንደሆንም ለወጣት አበበ ላቀረብኩለት ጥያቄ «የከተማው ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ አደራጅቷቸው የሚንቀሳቀሱ ጥቂት ወጣቶች እንደነበሩ አስታውሳለሁ:: እንቅስቃሴያቸው ግን ጎልተው ሊወጡ በሚችሉበት ደረጃ ነው ለማለት አያስደፍርም» የሚል ነበር ምላሹ::


በሙዚቃው ዘርፍ በተለይም በውዝዋዜ የተሻለ ነገር መኖሩን ግን አልሸሸገም:: ውዝዋዜና ዳንስ በግላቸው ከሚያሠለጥኑ መካከልም አንዱ እንደሆነም ገልጾልናል:: ማዕከሉም አሐዱ በሚል ስያሜ ይታወቃል::

ወጣቱ ችሎታውን የሚያወጣበትና አዕምሮውንም ዘና የሚያደርግበት መዋያ በበቂ ሁኔታ አለመኖሩ ለሥነምግባር መጓደል ዳርጎት ይሆን እንደሆነም ጠይቄው በሰጠው ምላሽ፤ ጎልቶ የሚነገር የሥነምግባር ጉድለት በአካባቢው ወጣት ላይ አለማየቱን ነው የገለጸው:: ለዚህም ማሳያ ብሎ የጠቀሰው፤ እርሱ ባቋቋመው የውዝዋዜና ዳንስ አሐዱ ማዕከል ውስጥ የሚሳተፉ የተለያዩ ወጣቶችና ታዳጊዎችን ሁኔታ ለማየት እድሉ ስላለው አብዛኞቹ መልካም የሚባሉ ሆነው ነው ያገኛቸው::

በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ችግር ያለባቸውን በተሻለ ለመቅረጽ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ከመጥፎ ምግባራቸው እንደሚመልሳቸው ነው የተናገረው:: በእርሱ ማዕከል ከሰለጠኑትም ጥሩ ደረጃ ላይ የደረሱ መኖራቸውን ያስታውሳል::



መምህር ወንድይፍራው ደጀኔ (ዶ/ር)



ወጣት አበበ ወልዴ



ፎቶ - ዳኜ አበራ

ወጣት ዱርሳ ሀሚን

‹‹ወጣቱ የማኅበረሰቡ ውጤት ነው:: ጓደኞቹ የሚውሉበትን ነው የሚያየው:: ያየውን ነው የሚከተለው:: ሌላ የሚውልበት ነገር ተመቻችቶለት ቢሆን ለምን እዚህ ቦታ ትገኛለህ ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል:: ስለዚህ ወጣቱን ልንወቅሰው አንችልም

ጫት ከመቃም ጋር በተያያዘ ወጣት አበበ በሰጠው አስተያየት፤ «ወጣቱ የማኅበረሰቡ ውጤት ነው:: ጓደኞቹ የሚውሉበትን ነው የሚያየው:: ያየውን ነው የሚከተለው:: ሌላ የሚውልበት ነገር ተመቻችቶለት ቢሆን ለምን እዚህ ቦታ ትገኛለህ ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል:: ስለዚህ ወጣቱን ልንወቅሰው አንችልም:: በእኔ እምነት ወጣቱ በመጥፎ ሊተረጎም የሚችል ነገርም እያሳየ አይደለም» በማለት ከጫት ጋር የማያያዙ ነገር የተሳሳተ እንደሆነ ያስረዳል::

ከከተማ አስተዳደሩ የሚጠብቀውንም በተመለከተ ቢያንስ በየቀበሌው ሁለት የወጣት ማዕከሎች ቢቋቋሙና በማዕከላቱም የወጣቱን ሥነምግባር ለማነጽም ሆነ በተለያየ ነገር ተጠቃሚ የሚሆንበት ነገር ቢፈጠር የተሻለ እንደሆነ ያምናል:: እርሱ እየሠራበት ያለውን የውዝዋዜና ዳንስ ጨምሮ በተለያየ መንገድ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ክበባት ቢጠናከሩና አዳዲሶችም ቢከፈቱ ወጣቱ መልካም የሆኑ ነገሮችን ለመሥራት ጠቀሜታው የጎላ እንደሚሆን ይገልጻል::

ከአካባቢውም ሆነ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን ሠላም ሁኔታን በተመለከተም ወጣት አበበ፤ ጥሩ ነገር ለመሥራትም ሆነ ለጥፋት ለመነሳሳት የወጣቱ ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ያምናል:: ለመጥፎ ድርጊትም ወጣቱን ለመጠቀም ጥረት የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩንም ይገነዘባል::

በድሬዳዋ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ወጣቱን ጨምሮ ማኅበረሰቡ የአካባቢውን ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ከአካባቢ ፖሊስ( ኮሚኒቲ ፖሊሲንግ) ጋር በመሆን አንድ ለአምስት ተደራጅተው የአካባቢያቸውን ሰላም ለማስጠበቅ እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ነው ያስረዳው:: ድሬዳዋ ፍጹም ሠላምና የፀጥታ ስጋት የማይታይባት እንደሆነችም ተናግሯል:: ሁሉም ለአካባቢው ዘብ ከቆመ ሀገራዊ ሠላም ይጠበቃል ::

ሌላው በከተማዋ ያገኘሁት ወጣት፤ በቅጽል ስሙ ዲጄ ዱስ ይባላል:: በዋና ስሙ ደግሞ ዱርሳ ሀሚን ተብሎ ነው የሚጠራው:: ወጣት ዱርሳ 25 ዓመቱ ነው:: ትምህርት ከ10ኛ ክፍል በላይ መዝለቅ ባለመቻሉ እራሱንና ቤተሰቡን ለመርዳት በሚያስችለው ሥራ ላይ እንደተሠማራ ይናገራል::

ወጣቱ ግለሰቦች፣ ተቋማት የተለያዩ ዝግጅቶች ሲኖሯቸው እንዲሁም ሠርግና ልደት በሙዚቃ በማጀብ ዲጄ ሆኖ ነው የሚሠራው:: በዚህ ሥራ ላይ የተሠማሩ የተለያዩ ሰዎችን በማየትና በጊዜ ሂደትም ፍላጎት አድሮበት ወደ ሥራው እንደገባ አጋጣሚውን አጫውቶኛል::

ለድሬዳዋ ወጣቶች የሚሆን የመዋያ ሥፍራዎችን በተመለከተም ወጣት ዱርሳ እንደነገረኝ፤ ለወጣቱ የሚሆኑ መዝናኛዎች ያንሳሉ:: አሁን ላይ ግን ለውጦች መታየት ጀምረዋል:: ለገሀሬ፣ አሸዋና በሌሎችም የከተማዋ አካባቢዎች ወጣቶች ተደራጅተው በተለይም በስፖርት በእግር ኳስ ሰፊ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው የከተማ አስተዳደሩ ጥረት እያደረገ ይገኛል::

በስፖርቱ ውስጥ የሚሳተፈው ብቻ ሳይሆን፤ ተመልካቹም መዋያ ማግኘት መጀመሩን ይገልጻል:: ወጣቱ በዚህ እንዲቀጥል ከተደረገ ለሱስ ተጋላጭነቱ እንደሚቀንስ፣ ሥራ ፈጣሪ ለመሆንም እንደሚነሳሳ፣ አካባቢውንና ሀገሩን የሚጠቅም ዜጋ ሊወጣ እንደሚችልም ወጣቱ አስረድቷል::

ከመዝናኛዎችም በእውቁ የኦሮሚኛ ዘፋኝ በክብር ዶክተር አሊቢራ የተሰየመው ፓርክ፣ እንዲሁም በከተማዋ እየተሠራ ያለው የስፖርት አካዳሚ ደግሞ ሲጠናቀቅ፣ ወጣቶቹ የተሻለ የጊዜ ማሳለፊያ እንደሚኖራቸው ተስፋ ያደርጋል::

ወጣት ዱርሳ፤ ከሠላምና ከፀጥታ ጋር ስላለው ሁኔታም አካባቢው ፍጹም ሠላም እንደሆነ፣ ነዋሪው 24 ሰዓት ያለ ሥጋት እየተንቀሳቀሰ መሆኑና እርሱም በሥራ አጋጣሚ እኩለ ሌሊት አልፎ ወደቤቱ የሚሄድባቸው አጋጣሚዎች የበዙ እንደሆነ ነው ያስረዳው::

በሌሎችም የሀገሪቱ አካባቢዎች ሠላም ተፈጥሮ ሀገር ከፀጥታ ሥጋት እንድትላቀቅ ተመኝቷል:: ወጣቱ በጀመረው ሥራ ውጤታማ ሆኖ ከራሱ አልፎ ለአካባቢው ወጣቶች የሥራ እድል ፈጥሮ ስኬታማ ለመሆን ነው ፍላጎቱ:: ይህንን ፍላጎቱን ለማሳካት ደግሞ በሥራው ሌትቀን እየተጋ እንደሆነም ተናግሯል::

የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲም በማኅበረሰብ አገልግሎት በአካባቢው ላይ ከሚያከናውናቸው ተግባራት ወጣቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሥራ ይገኝበታል:: በዚህ ረገድም ዩኒቨርስቲው እያከናወናቸው ስላለው ተግባር በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የማኅበረሰብ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እና የሶሻል ሳይንስ ትምህርት ክፍል መምህር ወንድይፍራው ደጀኔ (ዶ/ር) እንዳስረዱት፤ ወጣቶች መልካም ባሕሪ እንዲኖራቸው በተለያየ ክህሎትም ብቁ እንዲሆኑ ጥረት እያደረገ ይገኛል::

በሥነምግባር የታነጸና የተለያየ ችሎታ ያለው ትውልድ ለመፍጠር ከታች ጀምሮ መሥራት ይገባል የሚሉት ወንድይፍራው (ዶ/ር)፤ በተለይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ዩኒቨርሲቲው ትኩረት አድርጎ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ ነው የገለጹት:: ሀገር መውደድ ምን ማለት እንደሆነ፣ ወንድማማችነት፣ ተባብሮና ተዋድዶ በአንድ ላይ ስለመኖርና ተያያዥ በሆኑ ነገሮች ላይ ሥልጠና መሥጠት ከሥራዎቹ መካከል እንደሚጠቀሱ አስረድተዋል::

ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ቤተሙከራ ውስጥ(ላቦራቶሪ) እንዲጠቀሙ በማድረግና የሚጎላቸውንም ቁሳቁስ በማሟላት በትምህርታቸውም ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ሌላው ተግባር እንደሆነም አመልክተዋል::

እንደ ወንድይፍራው (ዶ/ር)፤ በቴክኖሎጂና በፈጠራ ላይ ያተኮረ ሥልጠናም በመስጠት ክህሎታቸው ከፍ እንዲል እንዲሁም በውድድር እንዲበረታቱ ይደረጋል:: እንዲህ ያለው መርሐግብርም በዩኒቨርስቲው የሚከናወነው ሳይንስ ወዳድ ትውልድ ለመፍጠር ታስቦ ነው:: በተለይም ሂሳብና ፊዚክስ ከባድ እንደሆነ አድርጎ የማየቱ ሁኔታንም ለመቀየር መርሐ ግብሩ ያግዛል ብለዋል::

ዩኒቨርሲቲው ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር በተያያዘም፤ ለአብነትም ከሥራና ክህሎት መሥሪያ ቤት ጋር በመሆን በሠሯቸው ሥራዎች የብሎኬት ማመረቻ ማሽነሪዎችን በመስጠትና በሥልጠናም እንደሚታገዙ የማድረግ ተግባራት እንደሚጠቀሱ ገልጸዋል:: የሥራ ማስጀመሪያ ግብዓቶችን ማሟላት፣ በሥልጠና ማገዝ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን መስጠት ጥሩ የሚባሉ ጅማሬዎች ቢኖሩም አጠናክሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል::

# የምድር በረከት

## የማዕድን ዘርፉ ያልተሻገራቸው ፈተናዎች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብት የታደለች ናት። በሁሉም የሀገሪቷ ክልሎች የተለያዩ የማዕድን ሀብቶች ይገኛሉ። ወርቅና የመሳሰሉት የከበሩ ማዕድናት፣ ፖታሽ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ሊቲየም፣ ታንታለም፣ ብረትና ብረትነክ ማዕድናትና ሌሎች ለኢንዱስትሪ እና ለኮንስትራክሽን ግብዓቶች የሚውሉ በርካታ ማዕድናት ይገኙባታል፡፡

ሀገሪቷ የእነዚህ ሁሉ ማዕድናት ባለቤት ትሁን እንጂ ማዕድናቱን አልምቶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተሠሩ ሥራዎች እዚህ ግባ የማይባሉና ብዙ መሰናክሎች መሻገር ያልቻሉ እንደሆነም ይነገራል። በተለይ ከሕገወጥነት እና ከፀጥታ ችግር ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮች ዘርፉን በእጅጉ እየፈተኑት መሆኑ ይስተዋላል።

ዘርፉ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ሰፊ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ ተደርጎ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩበት ቢሆንም፤ አገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት እንዳልተቻለ መረጃዎች ያመላክታሉ።

በአሁኑ ወቅት በማዕድን ዘርፉ 70 ፈቃድ የወሰዱና 134 በፍለጋ ላይ የተሠማሩ ባለፈቃዶች አሉ። ለ3286 የክልል ባሕላዊ ወርቅ አምራች ኢንተርፕራይዞች፣ ለሁለት የውጭ ባለሀብት እና ለሦስት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችም ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወደ ሥራ ተሠማርተዋል፡፡

በዘርፉ በኩባንያዎችና በኢንዱስትሪዎች አማካኝነት ለ145 ዜጎች እንዲሁም በባሕላዊ ወርቅ አምራች ኢንተርፕራይዞች ለ94 ሺህ 997 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።

እንደ ድንጋይ ከሰል ባሉ የማዕድን ልማት ጥሩ አፈጻጸም እየታየ ሲሆን፤ በዚህም ሀገሪቱ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር እያወጣች ከውጭ ታስመጣ የነበረውን የድንጋይ ከሰል በዚህ ልማት ማስቀረት ችላለች።

በማዕድን ዘርፍ የተሠማሩ በርካታ አምራቾች ያሉ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ ከዘርፉ ለማግኘት የታቀደውን የውጭ ምንዛሪ ማግኘት እንዳልቻለም ከማዕድን ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመላክታል ።

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረቡት የማዕድን ምርቶች የታሰበውን ያህል ገቢ ማግኘት እንዳልተቻለ ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ በስድስት ወራት ለውጪ ገበያ ከቀረቡ የማዕድን ምርቶች 243 ነጥብ 24 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ፤ 142 ነጥብ 978 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል። አፈጻጸሙም የእቅዱን 58 ነጥብ 7 በመቶ ነው። ለውጭ ገበያ የተላኩት ማዕድናት የወርቅ፣ የታንታለም፣ የሊቲየም ኦር፣ የጌጣጌጥና የኢንዱስትሪ ማዕድናት ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ 10 ክልሎች የወርቅ ማዕድን ሥራዎች በባሕላዊ መንገድ ይመረታሉ። ስድስት ወራት በኩባንያዎች ደረጃ ተመርቶ ወደ ብሔራዊ ባንክ ለማስገባት የታቀደው የወርቅ ምርት መጠን 2499 ነጥብ ዘጠኝ ኪሎግራም ሲሆን፤ 1445 ኪሎግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ማስገባት ተችሏል። በተመሳሳይ በባሕላዊ የወርቅ አምራቾች 1288 ኪሎግራም ወርቅ ለማምረት ታቅዶ፤ 431 ኪሎግራም የወርቅ ምርት ነው ለብሔራዊ ባንክ የገባው።

በባለፉት ስድስት ወራት ከወርቅ ምርት 227 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ፤ 134 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር ማግኘት ተችሏል። ይህ አፈጻጸም ከባለፉት ሦስት ዓመታት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የዚህ ስድስት ወራት አፈጻጸም ብልጫ አሳይቷል፡፡

ባሕላዊ የወርቅ አምራቾች ያመረቱት የወርቅ ምርት የኩባንያ የወርቅ ምርት ድርሻ አንጻር ሲታይ አነስተኛ መሆኑን የጠቆሙት ኢንጂነር ሀብታሙ፤ 77 በመቶ ያህሉ ወርቅ በኩባንያ ደረጃ እንዲሁም 23 በመቶ ያህሉ በባሕላዊ አምራቾች የተመረተ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ሚኒስትሩ፤ በስድስት ወራት በወርቅ ምርት ለማግኘት የታቀደውን ገቢ ለማግኘት ያልተቻለበት ዋንኛ



ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ

ምክንያት በክልል ደረጃ ያሉ አነስተኛ ፈቃድ ባላቸው አምራቾች በኩል ክፍተት መኖሩን አንስተዋል። ወርቅ ማምረት ላይ ምርት ችግር ሳይኖር ምርቱ እያለ ዋንኛ ችግር የሆነው ምርቱን ወደ ብሔራዊ ባንክ የማስገባት ችግር እንደሆነ አመላክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በፖታሽ ማዕድንም ኢትዮጵያ በደናክል ተፋሰስ ከ26 ቢሊዮን ቶን በላይ የፖታሽ ሃብት (resource) እና 540 ሚሊዮን ቶን የሚገመት የፖታሽ ክምችት (reserve) ከዓለም ግዙፉ ያልለማ የፖታሽ ክምችት ያላት አገር ናት ። ይህ ፖታሽ ለማዳበሪያና ለውጭ ገበያ (ለኤክስፖርት) የሚውል ነው። ይህን ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ሥራዎችም እየተሠሩ ይገኛሉ ፡፡

በድንጋይ ከሰል ማዕድንም ከ600 ሚሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ሃብት መኖሩን የሚናገሩት ሚኒስትሩ፤ አሁናዊ የሀገር ውስጥ ፍላጎት በዓመት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ቶን እንደሚጠጋ ያመላክታሉ። ከውጭ የሚገባው የድንጋይ ከሰል ምርትን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት ከ120 በላይ ሚሊዮን ዶላር ዓመታዊ ወጪ ማዳን መቻሉን አመላክተዋል።

በድንጋይ ከሰል ምርት ለሀገር ውስጥ ምርት አልፎ ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚችል ብዙ ክምችት አለ። ሆኖም ግን የድንጋይ ከሰል የራሱ የሆነ የጥራት መለኪያ ስላለው ከአመራረቱ ጋር ተያይዞ የጥራቱ ችግሮች ይነሳሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚፈልጓቸውን የጥራት መጠን ያለው የድንጋይ ከሰል ስለሚፈልጉ ይህንን የሚያሟላ ጥራት ያለው የድንጋይ ከሰል ምርት ማምረት እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ።

የድንጋይ ከሰል ጥራትን ለመጨመር የድንጋይ ከሰሉን የማጠብ ሥራ የሚሠራ ፋብሪካ እንደሚፈልግ ገልጸው፤ እንደ ሀገር እስካሁን ባለው ሁኔታ እሴት ጨምሮ የድንጋይ ከሰልን እያጠበ እያቀረበ ያለው አንድ ፋብሪካ ብቻ መሆኑን ይጠቁማሉ። በመሆኑም በሁሉም አቅጣጫ ያለው የሀገሪቱ የድንጋይ ከሰል ፍላጎትም በሚገባ በማወቅ ጥራት ያለው የድንጋይ ከሰል ማምረት እንደሚገባ አመላክተዋል።

በተጨማሪም እነዚህ እሴት ጨምረው የሚያቀርቡ ፋብሪካዎችንና ኢንቨስተሮችን ማበረታታት ይገባል። አሁን ላይ የድንጋይ ከሰል የሚያመርቱ አካላት እሴት እየጨመሩ ለሚያመርቱ ፋብሪካዎች የሚያቀርቡበት የአቅርቦት ሠንሠለት ማስተሳሰር የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ከተቋማት፣ ከማኅበራት እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ምክክር እየተደረገ መሆኑንም ነው ሚኒስትሩ የሚገልጹት፡፡

አሁን በሀገር ውስጥ የሚመረተው የድንጋይ ከሰል እሴት በመጨመር ጥራቱ በጠበቀ መንገድ ለውጭ ገበያ ለመላክ የሚያስችል ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ይህን በቅርብ በማሳካት የድንጋይ ከሰል ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚቻል መሆኑን ጠቁመዋል። ለዚህም እሴት በመጨመር የሚያመርቱ (ፕሮሰስ) የሚያደርጉ ኢንቪስተሮች ወደ ዘርፉ እንዲገቡ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ከፍተኛ መጠን ያለው የሲሚንቶ ክምችት ያላት ሀገር ናት ያሉት ሚኒስትሩ፤ በሲሚንቶ ምርት ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ከፍተኛ የምርት እጥረት አጋጥሞ እንደነበር አስታውሰው፤ ለዚህ ዋንኛ ምክንያት በአገሪቱ ላይ ተፈጥሮ በነበረው ጦርነት በዓመት ከሁለት ሚሊዮን ቶን በላይ ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡ ፋብሪካዎች ሥራ በማቆማቸው እንደሆነ አመላክተዋል።

‹‹አሁን ላይ ግን ቀደም ሲል ማምረት ያቆሙ ፋብሪካዎች ወደ ምርት እየመጡ፤ አዳዲስ ፋብሪካዎች ወደ ማምረት እየገቡ መሆናቸው ሲሚንቶ ምርት ተስፋ ያለው መሆኑን ያሳያል። አዳዲሶቹ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ማምረት ሲጀምሩ ደግሞ የተሻለ ማምረት ይቻላል። ለእነዚህ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚያስፈልገውን የድንጋይ ከሰል በበቂ ሁኔታ በሀገር ውስጥ የመተካቱ ሥራ መጠናከር ይኖርበታል።

በተያዘው በጀት ዓመት ሥራ ላይ ያሉት 11 የሲሚንቶ ፋብሪካዎች መሆናቸውን ገልጸው፤ ፋብሪካዎች በዓመት 14 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ የማምረት አቅም እንዳላቸው ተናግረዋል። ዓመታዊ የሀገር ውስጥ ሲሚንቶ ፍላጎት 36 ሚሊዮን ቶን ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ሦስት ነጥብ 51 ሚሊዮን ቶን ሲሚንቶ ተመርቷል። በዚህም የእቅዱን 83 በመቶ መፈጸም ተችሏል›› ነው ያሉት፡፡

በአገሪቱ አስተማማኝ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት ዋንኛው አስፈላጊ የሆነው ብረት መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፣ ለዚህ የሚያስፈልገው የብረት ማዕድን ሀብት እንዳለም ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት ‹‹አሁን ላይ የለሙት የብረት ምርቶች ብዙ አይደሉም፤ ገና ብዙ የሚቀራቸው ነገር በመኖሩ አልተጀመረም። አሁንም ብረት ላይ ትኩረት ተደርጐ እየተሠራ ሲሆን፤ ብረት ለተወሰነ ጊዜ ተግዳሮት ሆኖ መቆየቱ አይቀርም›› ብለዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት የማዕድን ኢንዱስትሪ ምርትን ለማሳደግ በተሠራው ሥራ 143 ሺህ 458 ቶን ብረት፣ 273 ሺህ የድንጋይ ከሰል መገኘቱን አስታውቀዋል። የግንባታ ግብዓት እጥረቶችን ለመፍታት ምርት ያቆሙ የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን ወደ ሥራ የማስገባት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በግራናይትና በማርብል ማዕድናት ምርት ጋር ተያይዞ ተስፋ ያለው ነገር እንዳለ ጠቅሰው፤ የፀጥታ ችግር ያለባቸው አካባቢዎች በተለይ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በአማራ ክልል የፀጥታ ችግር ሲስተካከል ምርት ማምረት እንደሚቻል አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ የበርካታ ማዕድን ሀብቶች ባለቤት ብትሆንም ከዘርፉ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ መሆን አልቻለችም ያሉት ሚኒስትሩ ፤ ሕገ-ወጥ ንግድ፣ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የሚፈጠሩ የፀጥታ መደፍረስ ችግር እንዲሁም ስለማዕድን ሃብት ያለው የግንዛቤ ማነስ፣ በቂ የሰው ኃይል እጥረት፣ በቂ የልማት በጀትና ቴክኖሎጂ አለመኖሩ ከማዕድን ሀብቱ ተጠቃሚ መሆን እንዳትችል አድርጓታል ሲሉ አስረድተዋል።

“ማዕድን ሀብቱ በራሱ የሚያመጣቸው ተግዳሮቶች አሉ። የፀጥታ ችግር በጣም አስቸጋሪ እየሆነ ያለው ይሄ ሀብት ባለበት አካባቢ ነው። የማዕድን ሀብት የሁሉም ኢትዮጵያውያን ሀብት በመሆኑ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በጋራ ተጠቃሚ በማድረግ የሀገር ኢኮኖሚን መገንባት ያስፈልጋል። ይህ ሀብት በሕገወጥ መንገድ ለሕገወጦች ሲሳይ መሆን የሌለበት ነውና ጥንቃቄ ያስፈልጋል” ያሉት ሚኒስትሩ፤ በተለይ አንዳንድ የፀጥታ ችግር ያለባቸው አካባቢዎች ለማዕድን ሥራ አዳጋች ቢሆንም በተቻለ አቅም ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አመላክተዋል።

ኢንቪስተሮች መጥተው በኢንቨስትመንቱ ላይ እንዲሠማሩ ሠላም መኖር እንዳለበት ሲያስረዱ፤ የማዕድን ኢንቨስትመንት ረጅም ጊዜን የሚፈልግ ሲሆን፤ ለአብነትም ወርቅ ለመፈለግ ብቻ አስር ዓመታት ሊፈጅ ይችላል። ለማምረት ደግሞ እንዲሁ ሌላ ሃያ እና ሠላሳ ዓመታትን ሊፈጅ ይችላል። ሲሚንቶ እና ነዳጅ ለማግኘትም ሆነ ለማምረት እንደዚሁ ረጅም ጊዜ ያስፈልጋል በዚሁ ሁሉ ጊዜም ሠላም ሊኖር ይገባል ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ እንደሀገር የማዕድን ዘርፉን የሚመራ ካውንስል ተቋቁሟል። ካውንሱሉ ብዙ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ግልጸኝነት፣ ተጠያቂነት፣ የአካባቢን ፀጥታ ሁኔታ የሚከታተል እና ዘርፉ የሚመራበት ሁኔታ የሚቆጣጠር ነው። ሕገወጥነት ለመከላከል በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋመው የማዕድን ካውንስሉ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ ሲሆን፤ በዘርፉ ያሉትን ችግሮች እየፈተሸ ይሠራል።

“ማዕድን ሲባል በተለምዶ የሚታወቀው ከወርቅ ያለፈ አይደለም። ማዕድን ወርቅ ብቻ አይደለም በርካታ ማዕድናት አሉ። ወርቅም ቢሆን አሁን ላይ እየተመረተ ያለው በባሕላዊ መንገድ ነው” ያሉት ሚኒስትሩ፤ በባሕላዊ መንገድ ወርቅ የአመራረት ሂደት በራሱ ጤነኛ ስላልሆነ ከፈቃድ አሰጣጡ ጀምሮ ለብዙ ሕገወጥ ነገሮች ተጋላጭ መሆኑን ይናገራሉ። ብዙ ሕገወጥ አካላት ያሉበት በመሆኑ ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲመጣ በማድረግ ማስተካከል እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ አሁን ላይ በወርቅ ምርት ለመሠማራት የሚፈልጉ ፋብሪካዎች ስላሉ እነዚህን በመደገፍ የሚጠበቀውን የወርቅ ምርት ማግኘት ይቻላል ሲሉ ተናግረዋል።

በማዕድን ዘርፍ በየደረጃው ያሉ ፍቃድ የሚሰጡ አካላት ኃላፊነት ስላለባቸው ተጠያቂነት የሚያሰፈን ሥርዓትን መከተል ይገባል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ዘርፉ ሙያዊ ሥነምግባር፣ ልምምድ፣ ኢንቨስትመንት እና ተከታታይነት ያለው ሥራን የሚፈልግ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

አሁንም የማዕድን ምርቶች በተለያዩ ደረጃዎች ቢመረትም ምርት ወደሚፈለገው አገልግሎት እየዋለ የታለመለትን ግብ እየመታ አይደለም ይላሉ። ባለፈው ዓመት በማዕድን ሕገወጥነት የተሳተፉ ብዙ የውጭ ሀገር ዜጎች ላይ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን አስታውሰው፤ አሁን ላይ መሻሻሎችና ለውጦች መኖራቸውን አመላክተዋል። ዘርፉ የአቅም ግንባታና የባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ ትብብር የሚፈልግ መሆኑን ገልጸዋል ።

‹‹ኮንትሮባንድ በሁሉም ዘርፍ ያለ የሀገር ችግር ነው›› ያሉት ሚኒስትሩ፤ አሁን ባለው ሁኔታ ወርቅ እና ማንኛውንም አይነት ማዕድናትን በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ማውጣት ብዙ ከባድ አለመሆኑን አንስተዋል። ኮንትሮባንድ በመከላከል ሕገወጥነት የመቀነስ ሥራ በማዕድን ሚኒስቴር ብቻ የሚሠራ ሳይሆን እንደሀገር ብዙ ሥራ መሥራትን የሚጠይቅ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## እብድና ዘበናይ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ጠዋት ከእንቅልፌ ነቃሁ፡፡ በሬን ስከፍት አንድ ምንዱባን የምጽዋት አቆፋዳውን ይዞ በሬ ላይ ቆሟል፡፡ "ስለማርያም" አለኝ፤ ፊቱን በማጣት አሳዝኖ፡፡ ቀኑ ማርያም መሆኑን እሱ ነው ያስታወሰኝ፡፡ ከአንድ እስከ ሰላሳ ያሉትን ቀኖች ዝም ብዬ ነው የምኖራቸው፡፡ ሰዎች ነጠላ ለብሰው በሰፈሬ ቀጭን መንገድ ወደ አጥቢያ ሲጎርፉ፣ እዛና እዚህ የተተከሉ የአምልኮ መቅደሶች ጡሩንባቸውን ሲያሰሙኝ ምንም ያልመሰለኝ በዚህ ሰው ደጄ መቆም ብዙ መሰለኝ፡፡ የኖርኳቸውን አርባ ስድስት አመታት እንዴት መጥተው እንደሄዱ እንኳን አላውቃቸውም፡፡ ዝም ብሎ መኖር ይቻላል?

"ስለማርያም!" ማጣት የደቆሰውን ኮሳሳ ድምጹን ደገመልኝ፡፡

አሁን እኔ ምን አለኝና በሬ ላይ ይቆማል? ከዛች እመበለት የባስኩ፣ ከመቀነቴ ፈትቼ የምሰጠው ስሙኒ የሌለኝ መሆኔን ቢያውቅ፡፡ ቦሀቃና ገንቦዬ ዘይትና ዱቄት አጥተው ለዘመናት እንደከረሙ ቢገባው በጠዋት ደጄ አይቆምም ነበር፡፡ ግቢያቸውን በግንብ ያጠሩ የጎረቤቶቼን በር አልፎ እኔ ዘንድ መምጣቱ ሞኝ ለማኝ እንደሆነ እንዳስብ አደረገኝ፡፡ ይሉኝታ ይዞኝ እንጂ እኔም ልመና ልወጣ አንድ ሀሙስ የቀረኝ ነኝ፡፡ "ምን ይሉኝ"ን ፈርቼ እንጂ በህይወቴ ውስጥ ጨርቅ አስጥለው የሚያስኬዱ ብዙ ጉስቁልናዎች አሉ፡፡ እንዳይታዩ ሸፍኜአቸው እንጂ . . . እንዳይገለጡ ደብቄአቸው እንጂ እንዳንተ እና ከአንተ የባስኩ ነኝ አልኩት . . በሆዴ፡፡ ግን ምን ታይቶት ጎበኘኝ?

"ሂድ"ልለው ቃጣኝ፡፡ አይደለም ላንተ ለራሴም የምበላው የለኝ ልለው፣ ሄደህ ከሞላቸው ለምን ልለው አፌን አሞጠሞጥኩ፡ ፡ ከአንደበቴ ግን ቃል አልወጣም፡፡ ልለው ያሰብኩትን የሻረ ሌላ አመክንዮ ውስጤ ተፈጠረ፡፡ ዝም ብዬ አስተዋልኩት ... እስካሁን ያልታየኝን ነገር አየሁ፡፡ ከፊት ለፊቱ ደረቱ ላይ የቤዛይተ ኩሉን ምስል አንጠልጥሏል፡፡ በግራው ቅዱስ ገብርኤል፤ በቀኙ ደግሞ ቅዱስ ሚካኤል ከመስቀልና ጎራዴአቸው ጋር፡፡ በዚህ ማዶ አናኒያና አዛርያ ምሳኤል እሳቱ መሀል ከጸጉራቸው ላይ አንዲት ሳይጎድል . . በዛ ማዶ ትዕቢተኛው ሳጥናኤል በመላኩ ተረግጦ . . . መሀል ላይ አማላጅቱ፡፡ ይሄን ኩነት ማምለጥ አልቻልኩም፡ ፡ በእምነት የበረቱ ዓይኖቼ ከመላዕክቶች አንዱን መስለው አስፈሩኝ፡፡ እንደምንም አየሁት፡፡ ማጣት ሰው ቢሆን ኖሮ . . . ድህነት አካል ነፍስ ቢለብስ ኖሮ ይሄን ሰው ይሆን ነበር፡፡ ባደፈ ገላ . . . ባልጠራ ደምግባት ረህጦ አገኘሁት፡፡ በሰለለ ገላ . . በከሰለ ሰውነት ይሄን የሚያህል እምነት ይቻላል? ነው፣ ወይስ በእምነቱ የማይጨክነውን ሕዝብ በዘዴ ሊበዘብዝ አስቦ ያደረገው? በየቱም እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ እንደ ምንም ብዬ ሃሳቤን ወደ መጀመሪያው አስጠግቼ "አማኝ ነው" ስል ተቀበልኩት፡፡

በእለተ ማርያም በልመና ከበሬ የቆመን ምስኪን የለኝም ብሎ ማባረር ዳግመኛ የማይመጣን እድል ሂድ ከዚህ ማለት መሰለኝ፡ ፡ በላኤ ሰብን ሆኜ በዚህ ሰው ችግር እንደ ዳክሮስ ከማንም ቀድሜ ገነት ልገባ ቤዛይተ ኩሉ ይሄን ችግረኛ በጠዋት የላከችልኝ መሰለኝ፡፡ ግን እንዴት መሰለኝ? ትውልድ ሁሉ ብጽእት የሚሏትን ንጽእት፣ ከእብራውያን ቆነጃጅቶች የራቀችውን እመቤት፣ ገብርኤል ያበሰራትን፣ ኤልሳቤት የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እንደምን ይሆንልኛል? ያለቻትን ሴት መራቄ . . መናቄ . . መርሳቴ . . መግፋቴ ከዓለም ወንበዴ ዋነኛው እንደሆንኩ ተገለጠልኝ፡፡

ይሄን ሰው መግፋት ፈጣሪን ከበር ላይ ማባረር ሆነብኝ፡፡ ያ ባለከዘራው እየሱስ በዚህ ሰው ምስል በሬ ላይ ሆኖ ክፈትልኝ እያለኝ ቢሆን በምን አውቃለው? ያ ማንም በሩን ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ ለመግባት ዝግጁ ነኝ ያለው አምላካዊ ቃል በእኔ ላይ ሊገለጥ ይሄን ሰው እንደ ሰበብ ተጠቅሞ ቢሆንስ? ሆነም አልሆነ ከመስጠት ውጪ አማራጭ የለኝም፡፡ ግን ምንም የለኝም፤ ምንድነው የምሰጠው? ወደ ኋላዬ ተመልሼ ለዘመናት የማውቃትን ቤቴን በዓይኔ በረበርኳት፡፡ የሆነ ቦታ የሆነ ነገር ያስቀመጥኩ ይመስል የማውቀውን ታሪኬን እንደማላውቀው ሆኜ መፈተሽ ጀመርኩ፡፡ ምንም አላገኘሁም፡፡ ሰዎች የሚያውቁኝ በሁለት ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያው ግዴለሽ በመሆኔ ሲሆን፤ ቀጥሎ ለዘላለም እያፈራረቅሁ በምለብሳቸው ሁለት ሸሚዞቼ ነው፡፡ ግዴለሽነቴን ልሰጠው አልችልም፡፡ ከሸሚዞቼ አንዱን ልሰጠው ግን እችላለሁ፡፡

ለሰባት ዓመታት ያለማቋረጥ የለበስኳትን አንድ ለእናቱ መቀየሪያዬን ሽቶ ነስንሼ ዘረጋሁለት፡፡

ተቀበለኝ . . .

ለምርቃት ከጭንቅላቱ አጎነበሰ፡፡ ያስደሰትኩት አልመሰለኝም፡፡ እርካታን ከሳቅ ጋር ስመትር የኖርኩ አለሌ ነኝ፡፡ በዳመነ ፊቱ ላይ ሳቅን ሳጣ ጊዜ ስጦታዬ መናኛ እንደሆነ እንዳስብ አደረገኝ፡፡ ደማቅ ሆነ ፈዛዛ ሰው ያለውን ከሰጠ ሰጠ ነው ስል ራሴን ለማበረታት ሞከርኩ፡፡ ህይወቴን እንደሰጠሁት ቢያውቅ፡፡ ታሪኬን . . . ማንነቴን እንደሰጠሁት ቢረዳ ተመኘሁ፡፡

የህይወት ታሪኬ ቢጻፍ ግዴለሽነቴና እነዚህ ሁለት ሸሚዞች ጥሩ መታወሻዬ እንደሚሆኑ አምናለሁ፡፡ ከመታወቂያ ስሜ እኩል ‹ያ ግዴለሹ› መለያዬ ነው፡፡ በብዙ ንፉግ ባለጸጎች መሀል ቆማ ትዳሯን እንደሰጠችው እንደዛች እመበለት ህይወቴን ሰጠሁት . . . ታሪኬን ዘረጋሁለት፡፡ ትዝታዬን . . . ትውስታዬን እነሆ አልኩት፡፡

ልክ እንደ ሸሚዞቼና ግዴለሽነቴ ሰው በመኖር ውስጥ የተለማመደው በእድሜ ሃዲድ ስር የተገኘ የህይወት ታሪክ አለው፡ ፡ በጨሌና በቅቤ እንደምንካድመው ባዕድ አውለያ የምንካድመው ባዕድ ማንነት፡፡ ከለበስኳት ሸሚዜ ጋር ብቻዬን ቀረሁ፡፡ ምስኪኑ ታሪኬን ይዞብኝ ሲሄድ ቆሜ አየሁት፡፡ ከእግሩ አንከስ ይላል፡፡ አቆፋዳውን ያዘለ ትከሻው ወደ አንድ ጎን አጋድሏል፤ ምስቅልቅል ሰውነት፡፡ ለረጅም ሰዓት አየሁት . . . ጀርባው ላይ ያላስተዋልኩትን አስተዋልኩ፡፡ እንደፊትለፊቱ ጀርባውም በጎለጎታው እየሱስ ስዕል ያጌጠ ነበር፡፡ ሳልሰጠው ሰድጄው ቢሆን በዚህ ምስል ፊት እንዴት እጸና ነበር? ካለመኖር የከፋው ሞት ይሄ አይደል . . . በትልቅ እምነት ውስጥ ቦታ ማጣት?

እንኳንም ሰጠሁት፡፡ በህይወቴ ከሰራሁት በጎ ሥራ ሁሉ ለዚህ ሰው መስጠቴ ልክ ሆኖ ተሰማኝ፡፡ እየሱስን በመስቀል ላይ ጀርባው ላይ አየሁት፡፡ እናቱ ማርያም በሀዘን ወደ ላይ አንጋጣ፣ የቀሎጲያ ሚስት ማርያም፣ ሌላኛዋ መቅደላዊት ማርያም ከዮሀንስ ጋር በአንድ ወደ ጌታ ሞት አንጋጠው ሲያነቡ . . . ሌንጊኖስ ጎኑን ሲወጋው . . . በጦሩ በኩል እውር አንድ አይኑ ስትበራ፣ አይሁዶች በለው፣ በለው ሲሉ፣ ጲላጦስ ከደሙ ንጹህ ነኝ ሲል በዛ ጀርባ ላይ አየሁ፡፡ ሳልሰጠው ቀርቼ ቢሆን . . .

በአራስ ጀምበር ፊት ታሪኬን ቀምቶኝ በሚሄድ ድሃ ዳና ላይ በሬን ተደግፌ እንደቆምኩ ከርቀት ኃይለኛ ጩኸት ሰማሁ፡ ፡ ወደ ቤቴ ሳልገባ ወደ ጩኸቱ ተራ ተጣደፍኩ፡፡ ታሪኬን የወሰደብኝን ድሀ ሲንደፋደፍ ከመንገድ ቀድሜው ወደ ላይ ሰፈር ፈጠንኩ፡፡ በአራቱም የሰፈራችን አቅጣጫ ወደ ጩኸቱ ቦታ ሰዎች ሲተሙ አደገኛ ነገር መፈጠሩን ልቤ ጠረጠረ፡፡ ቦታው ላይ ደረስኩ . . . ቀድመውኝ ከደረሱ ከማውቃቸውና ከማላውቃቸው የሰፈሬ ሰዎች ጋር ተደባለኩ፡፡ በእድሜ ገፋ ያሉ የሰፈራችን አባት በጎረምሳ የፊጥኝ ወደ ተያዘችው ሴት ጠጋ ብለው "ምን ሆነሽ ነው?" አሉ፡፡

"ሸበቴን ነቅሎብኝ፡፡ እርጅና እንደምጠላ እያወቀ እንዴት ሸበቴን ይነቅላል? ይሄ ውሻ! ልቀቀሉኝ ልዘልዝለው" ስትል ከጎረምሶቹ ለማምለጥ ታገለች፡፡

"የምን ሸበት?" ሽማግሌው ጠየቁ፡፡

"ሸበት ነዋ! ያለ እድሜዬ እንዳረጅ፣ ይቺ አሮጊት እያሉ ጎረምሶች እንዲጠቋቆሙብኝ . . . ቆሞ ቀር ሆኜ እንድቀር ፈልጎ አይደል የነቀለብኝ?"

"እረ ባክሽ ተይ! ይሄ አንድ ፍሬ ልጅ ስለምታወሪው ምን ያውቅና ነው እንዲህ የምትይው?" አሉ ልጁን ሸሽገው የያዙት አንድ እናት፡፡

ወደ ልጁ እየጠቆመች "ይሄ ነው የማያውቀው? የልደት ካርዱን አስፍቆ እንጂ የሰፈሩ የእድሜ ባለጸ ጋ ነው፡፡ እንዳውም እናገራለሁ፤ አብረሽኝ ካልተኛሽ እያለ እያስቸገረኝ ነው" ስትል ምራቋን ቱ አለችበት፡፡ ምራቋ ኢላማውን ስቶ ካሰበችበት ሳይደርስ ሌላ ሰው ደረት ላይ አረፈ፡፡

‹አበስ ገበርኩ› አሉ የቅድሟ ሴት፡፡

"እብድና ዘበናይ የልቡን ይናገራል" አድራሻው ከየት በኩል እንደሆነ ያላወኩት ድምጽ ወደ ጆሮዬ ተወናጨፈ፡፡

‹የገዛ ልጇን ነው እንዲህ የምትለው?› አጠገቤ የቆመ ወጣት ፊት ፊቴን እያየ ጠየቀኝ፡፡

እኔ በተጠየኩት ጎረቤቷ ናት መሰል ጓዳ ጎድጓዳዋን የምታውቅ በሚመስል አኳኋን ‹ለዛውም የመጀመሪያ ልጇ ነዋ! እሱን ከወለደች በኋላ ነው እንዲህ እቅሏን የሳተችው› ስትል ከነማብራሪያው ከበስተኋላዬ መለሰችለት፡፡ መልኳን ላየው ወደ ኋላዬ ስዞር በነጠላ ተከናንባለች፡፡

ከዚህ ንግግሯ በኋላ አብዛኛው ሰው እየተዋወት ሄደ፡፡ ቀስ በቀስ ግቢው ርቃኑን ቀርቶ እኔና አንቀዋት የያዟት ሶስት ሰዎች ከአንድ አሮጊት ጋር ቀረን፡፡

እኔም መሄድ ስላለብኝ ግቢውን ለቅቄ ስወጣ የቅድሙን ድሀ ጎዳናው ላይ አገኘሁት . . . እያነከሰ፡፡ ከመቼው ሸሚዜን እንደለበሳት እንጃ ታሪኬን አዳፋ ገላው ላይ አየሁት፡፡ አልፎኝ ሲሄድ ቆሜ አየሁት . . .

..........

አንዳንድ ጊዜ ሰው አለመሆን ቢኖር፡፡ የሆነ ነገራችንን ረስተንበት የምንመለሰው ሌላ ተፈጥሮ ቢኖር፡፡ እንደ ንስር ለአፍታ ተሰፍረን በብርታት ለምን ጊዜም ሰው ብንሆን፡፡ በማስተዋል ነጻነትን ማምጣት ሲያቅተኝ እንዲህ በማሰብ በነጻነት መኖር ያምረኛል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ኔታንያሁ ሐማስ ያቀረበውን የተኩስ አቁም ስምምነት ቅድመ ሁኔታ ውድቅ አደረጉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤኒያሚን ኔታንያሁ ሐማስ ያቀረበውን የተኩስ አቁም ስምምነት ሃሳብ በወራት ውስጥ በጋዛ "ሙሉ ድል መቀዳጀት" ይቻላል በማለት ሳይቀበሉት ቀሩ።

ኔታንያሁ ይህን ያሉት አዲስ ለቀረበው የተኩስ አቁም ስምምነት ምላሽ ለመስጠት ሐማስ ጥያቄዎች ማቅረቡን ተከትሎ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከቡድኑ ጋር የሚካሄድ ድርድር "የትም አይደርስም" ያሉ ሲሆን ሐማስ ያቀረበውን ጥያቄም "አስገራሚ" ብለውታል።

በሁለቱ ወገኖች መካከል የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረስ አሁንም ንግግሮች እንደቀጠሉ ነው።

ሆኖም ኔታንያሁ ረቡዕ ዕለት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ " ከድል ውጪ ሌላ አማራጭ የለም" ሲሉ ተናግረዋል።

"ሐማስ በጋዛ ነፍስ እንዲዘራ የምንፈቅድ ከሆነ በቀጣይ ለሚፈፅመው ጭፍጨፋ ጥያቄው የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው የሚሆነው" ብለዋል።

እስራኤል ሐማስ ላቀረበው ሃሳብ አዎንታዊ ምላሽ ትሰጣለች ተብሎ ተጠብቆ የነበረ ቢሆንም ሳትቀበለው ቀርታለች።

የእስራኤል ባለሥልጣናትም ሐማስ በራሱ ጊዜ ጦርነቱን ለማስቆም የሚያደርገውን ጥረት ተቀባይነት የሌለው አድርገው ተመልክተውታል።

የሐማስ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሳሚ አቡ ዙሁሪ ለሮይተርስ የዜና ወኪል እንደተናገሩት፤ የኔታንያሁን ንግግር " "ፖለቲካዊ ድፍረት" ያሉ ሲሆን ፤ይህም በቀጣናው ያለው ግጭት እንዲቀጥል ያላቸውን ፍላጎት የሚያሳይ ነው ብለዋል።

አንድ ግብጻዊ ባለሥልጣን በግብፅ እና በኳታር አደራዳሪነት በአዲስ ዙር የሚካሄዱት ድርድሮች በካይሮ እስከ ትናንትና ድረስ እንደሚቀጥሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ግብፅ ሁለቱ ተፋላሚ አካላት ስምምነት ላይ ለመድረስ ግትርነታቸውን እንዲተው ጥሪ ማቅረቧንም እኚሁ የቢቢሲ ምንጭ ገልጸዋል።

ኔታንያሁ " ቅዠት" ያሉትን እቅድ ሳይቀበሉት መቅረታቸው የሐማስ ምላሽ 'አዎንታዊ' መሆኑን ከገለጸችው የኳታር አስተያየት ጋር ተቃርኗል።

ሐማስ ለቀረበለት የተኩስ አቁም ስምምነት ቅድመ ሁኔታውን ያስቀመጠው ማክሰኞ ዕለት ነበር።

ሮይተርስ የዜና ወኪል የተመለከተው የሐማስ ረቂቅ ሰነድ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች በምዕራፍ ከፍሎ አስቀምጧል።

በምዕራፍ አንድ የ45 ቀናት የተኩስ አቁሙ ፋታ ሁሉም የእስራኤል ሴት ታጋቾች እና ከ19 ዓመት በታች የሆኑ ወንዶች፣ አረጋውያንና ሕሙማን በእስራኤል እስር ቤት ውስጥ ካሉ ፍልስጤማዊ ሴቶች እና ሕጻናት ጋር ልውውጥ እነደሚደረግ ሐማስ አሳውቋል።

የእስራኤል ኃይሎችም በጋዛ በርካቶች ከሚኖሩባቸው አካባቢዎች ለቀው ይወጣሉ። ከዚህም በተጨማሪ በግጭቱ የወደሙ ሆስፒታሎችን እና የተፈናቃይ ካምፖችን መልሶ የመገንባት ሥራ ይጀመራል ላል የሐማስ ምዕራፍ አንድ ዕቅድ።

በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የቀሩ የእስራኤል ወንድ ታጋቾች ከፍልስጤማውያን እስረኞች ጋር ልውውጥ ይደረጋል ። የእስራኤል ኃይሎችም ሙሉ በሙሉ ጋዛን ለቀው ይወጣሉ ብሏል።

በምዕራፍ ሦስት እንዲሁ ሁለቱ ወገኖች አስከሬኖችን ይለዋወጣሉ፤ የሚል ውጥን አስቀምጧል፤ የቀረበው ረቂቅ ስምምነት ለጋዛ የሚቀርበው ምግብ እና ሌሎች ሰብዓዊ እርዳታዎች አቅርቦት እንዲጨምርም ይጠይቃል።

በ135 ቀናቱ የተኩስ አቁም ፋታም ጦርነቱን ለማስቆም የሚደረገው ድርድር እንደሚጠናቀቅም ሐማስ ገልጿል።

ሐማስ ባለፈው የአውሮፓውያኑ ዓመት ጥቅምት ወር ላይ በደቡባዊ እስራኤል በፈፀመው ጥቃት አንድ ሺህ 300 የሚሆኑ ሰዎች ተገድለዋል።

እስራኤል ለዚህ ጥቃት የአጸፋ ርምጃ መውሰድ ከጀመረች በኋላም በርካቶች የተገደሉ ሲሆን የተኩስ አቁም ስምምነቱ ተግባራዊ ካልሆነም ሌሎች ጥቃቶች እንደሚቀጥሉ ይገመታል።




ቀደም ብሎ እስራኤል፣ አሜሪካ፣ ካታር እና ግብፅ አቀረቡት የተባለው የተኩስ አቁም ስምምነት ይዘት ለሕዝብ ይፋ አልሆነም።

ነገር ግን የተኩስ አቁም ስምምነቱ ለስድስት ሳምንታት እንደሚቆይና ሐማስ የታገቱ እስራኤላዊያንን የሚለቅ ከሆነ ፍልስጤማዊያን እስረኞች በምትኩ እንደሚለቀቁ ተነግሯል።

አሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንተኒ ብሊንከን፤ ሐማስ ስለሰጠው ምላሽ ከእስራኤል ባለሥልጣናት ጋር እንደመከሩ ገልጸዋል።

ብሊንከን የሐማስን ምላሽ አሜሪካ እንዴት እንደምትመለከተው ባይገልጡም ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን "ትንሽ ከበድ ያለ" ሲሉ መግለፃቸው የሚታወስ ነው።

ባለፈው ኅዳር አንድ ሳምንት በቆየው የተኩስ አቁም ስምምነት ታግተው የነበሩ 105 እስራኤላዊያንና የሌሎች ሀገራት ዜጎች ሲለቀቁ በእስራኤል እሥር ቤቶች የነበሩ 240 ፍልስጤማዊያን ተለቀዋል።

በእስራኤል እና ሐማስ መካከል የሚደረግ የተኩስ አቁም ስምምነት የመካከለኛው ምስራቅን ውጥረት ለማርገብ አንዱ መፍትሔ እንደሆነ አሜሪካ በተደጋጋሚ ገልጻለች።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## በእርቅ ዘላቂ የአብሮነት ቤታችንን እንሥራ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሀገር የማንነት ዓውድ ናት..ሕዝብ ደግሞ የዚህ እውነት መቋጫ። በአንድ እጅ ላይ እንዳሉ እንደ መዳፍና አይበሉባ እኩል የሚጠሩ..እኩል የሚወሱ። ይሄ ሁሉ የማንነት ጉራማይሌ መልክ ብዙኃነትን ታቅፎ በእያንዳንዳችን ማንነት ላይ እንዲንጸባረቅ የሆነው በሀገርና በሕዝብ ስም ነው። ይሄ ሁሉ የታሪክና የባሕል፣ የሥርዓትና የሉዓላዊነት ውሕድ ኅብረብሔራዊት ሀገር የሠራው ተለያይተው በተመሳሰሉ፣ ተመሳስለው በተለያዩ ብዙ አይነት መልኮች ነው፡፡

ጥንት በእያንዳንዳችን የመንፈስና የሥነልቦና ባሕር ውስጥ ኢትዮጵያዊነት መሠረቱን ሲጥል ኅብረትና አንድነትን ተንተርሶ ነው። አንድነት ብዙኃነትንና ባለታሪክነትን..ጀግንነትንና ሉዓላዊነትን አላበሰን። በስተመጨረሻም የነፃነት ፋና ወጊ፣ የፍትሕና የሚዛናዊነት በኩሮች ሆንን። ለአፍሪካ የነፃነት ትግልና አቅምና መነቃቃት መሠረት ሆንን ፡፡

ዛሬም ድረስ አፍሪካ በእኛ የነፃት ገድል አንገቱዋን እንዳቀናች ነው። ዛሬም ድረስ ዓለም በእኛ የታሪክ እና የጀግንነት ጀብድ የምትደነቅ ናት። ይሄ ስም..ይሄ ማንነት እንዴት መጣ? ብለን ስንጠይቅ አንድነትን የለወሰ የሠላም ባለቤትነትን እናገኛለን። አብሮነትን ከኢትዮጵያዊነት ጋር የገመደ፣ የቋጠረ ማንነትን እናገኛለን፡፡

ይሄ የድሮ መነሻችን ነው። አሁናዊ እኛነታችን መልኩን ቀይሮ ብቻነትና እኔነትን የሚያቀነቅንበት ሆኗል። የዛሬ ስሞቻችን እንደድሮው መልከ ደማም ወይም ደግሞ ኢትዮጵያዊነት የደመቀባቸው አይደሉም። በብሔርና በጎሳ፣ በጎጥና በእኔነት ወይበው ደብዝዘዋል።

የታሪኮቻችን መሐሉ የብዙኃነት ምሰሶ የቆመበት ነው። ለብቻ አስበን፣ ለብቻ ተራምደን ያቆምነው መሠረት የለም። የኢትዮጵያዊነት ጣሪያ በአብሮነት ክንድ የተደገፈ ለመሆኑ ማስረጃ አያስፈልገውም። ተያይዘንና ተቆላልፈን የመጣንባቸው የታሪክና የማንነት ዳናዎች ዛሬም ሳይደበዝዙ ምስክሮች ናቸው።

ወደኋላ ባየን ቁጥር እነዛን ብዙ አንድ አይነት እግሮች የረገጧቸውን፣ ብዙ አንድ አይነት እጆች የጨበጧቸውን የማንነት ማኅተሞች ነው የምናገኘው። እነዚህ ክንዶች አሁን ላይ ዝለዋል። ኢትዮጵያዊነትን ሳይሆን እኔነትን የሚናገሩ ሆነው ፈርጥመዋል። ወደተውነው ወደጥንቱ የአብሮነት ማዕድ እስካልተመለስን ድረስ ትንሳኤያችን ሩቅ ነው።

በመነጋገር ቤት ካልሠራን፣ በውይይት ወደእርቅና ወደአብሮነት ካልተሸጋገርን መጪው ጊዜ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው። አይደለም በጥላቻና በመለያየት ቀርቶ በፍቅር ተጉዘን እንኳን ሩቅ በማንደርስበት ጊዜና ዘመን ላይ ነን፡፡

በብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን አሰናጅነት ላለፉት ዓመታት ዝግጅት የተደረገባቸው የምክክር መድረኮች እየጠበቁን ነው። በሰከነና በረጋ መንፈስ ሀሳብ ሰጥተን ሀሳብ በመቀበል፣ ችግሮቻችን ወደማያንሠራሩበት ደረጃ ማሸጋገርን ቀጣይ ዕጣ ፈንታችንን የሚወስን ጉዳይ ነው። ሀገራችንን በአዲስ አስተሳሰብ፣ በአዲስ የፖለቲካ ርዕዮት ማረቅ ካልቻልን ችግሮቻችን “ከድጡ ወደማጡ” እየሆኑ የሚታደገን አይኖርም። የኛ ቀርቶ የመጪ ትውልዶችም ዕጣ ፈንታ ታሳቢ አይሆንም፡፡

ትላንትና ዛሬም ጭምር ለዓለም ሠላም አስተዋፅዖ ያደረገች ሀገር፣ ትላንትና ለአፍሪካ መነሳት መንገድ የጠረገ ሕዝብ ዛሬ ሠላም አጥቶ፣ ፍቅርና አንድነት፣ እርቅና ተግባቦት ርቀውት ሠላም ፈላጊ ሲሆን ማየት አሳዛኝ ነው። የቱጋ ነው የተበላሸነው? የቱ ጋ ነው ርካብ የሳትነው? ዘመናትን ተጋምደን፣ ተሳስረን የመጣን ሕዝቦች ምን ነፈሰብን? ማን ቦደነን? እነኚህን ጥያቄዎች በመንተራስ ወደመፍትሔዎቻችን ልንጓዝ ይገባል፡፡

በሠላም እጦት፣ ባለመግባባት፣ በሥልጣን ሽኩቻ ብዙ ትላንትናዎች አልፈውናል። በዘረኝነት፣ በመገፋፋት፣ በኃይል እና በእልህ እሳቤ እልፍ ትናንቶችን መጥተናል። ታሪክ በማጣመም፣ ያለፈን በማስታወስ እልፍ ቁርሾዎችን ፈጥረናል። አብሮነትን በማኮሰስ፣ እኔነትን በማንገስ በውበታችን ላይ መለያየትን ዘርተናል። የቀረን ምንድነው? የቀረን በመነጋገር መግባባት ብቻ ነው። በእርቅና በምክክር ወደተውነው መመለስ ነው፡፡

በእርቅ የአብሮነት ቤት መሥራት የዚህ ትውልድ የቤት ሥራው ነው። መፍትሔ አዘል ሀሳቦቻችን ለፈረሰ ጎጇችን፣ ላዘመመ አብሮነታችን ዋልታና ማገር ነው። ያን ማንም የሌለውን የፍቅርና የአንድነት ጥንተ ጠዋታችንን ለመመለስ ከእያንዳንዳችን የሚዋጣ የሀሳብ መዋጮ አለ። ያን ማንም የሌለውን የብኩርና ፊተኝነት ለመመለስ ከሁላችን የሚጠበቅ የይቅርታና የመተው ምንዳ አለ።

ሀገርና ሰው..ሰውና ሀገር የታሪክ መልኮች ናቸው። በፍቅር ካልሆነ በእንዴትም አያብቡም። አሁናዊ ፉክክራችን የከረመ ፍቅራችንን እንዳያደበዝዝብን ኢትዮጵያ የምትቀድምበት የታሪክና የፖለቲካ ምሕዳር ያስፈልገናል። በታሪክ ውስጥ ትልቁ የትውልድ ክስረት የፉክክር ፖለቲካ ነው። ከመውደቅ ባለፈ ተፎካክረን ያላሸነፍንባቸው ብዙ የታሪክ ገጾች አሉን። አሁንም በዛ መንፈስ ውስጥ መሆናችን ነገን እንድንሰጋ ያደርገናል፡፡

የውይይት ትልቁ ፀጋ እልኸኝነትና የኃይል አማራጮች ሊያስከፍሉ የሚችሉትን ያልተገባ ዋጋ ማስቀረት ነው። ፍርሀትና ስጋት ባንጃበቡባት ሀገር ላይ ዝምታና ድንግርታ ጥቅም የላቸውም። ትኩሳቶቻችን እንዲበርዱ፣ የሰላም መቅረዞቻችን ሩቅ እንዲያበሩ ስለሠላም የሚያወሩ አፎች፣ ስለአንድነት የሚሰብኩ አንደበቶች መብዛት ግድ ይላቸዋል። ጋን በጠጠር እንዲሉ..ከማንም ምንም ሳንጠብቅ ያለንን ትንሽ በማዋጣት ትልቁን ጋን ማቆም እንችላለን።

> ሀገርና ሰው..ሰውና ሀገር የታሪክ መልኮች ናቸው። በፍቅር ካልሆነ በእንዴትም አያብቡም። አሁናዊ ፉክክራችን የከረመ ፍቅራችንን እንዳያደበዝዝብን ኢትዮጵያ የምትቀድምበት የታሪክና የፖለቲካ ምሕዳር ያስፈልገናል። በታሪክ ውስጥ ትልቁ የትውልድ ክስረት የፉክክር ፖለቲካ ነው። ከመውደቅ ባለፈ ተፎካክረን ያላሸነፍንባቸው ብዙ የታሪክ ገጾች አሉን። አሁንም በዛ መንፈስ ውስጥ መሆናችን ነገን እንድንሰጋ ያደርገናል

በሀገራችን ጉዳይ ላይ እኩል ተሳታፊነት እኩል ተጠቃሚነትን ያመጣል። መነሻችን ብዙኃነት እንደሆነ መድረሻችንም ኅብረብሔራዊነት ነው። በጋራ ካሰብን የጋራ መፍትሔ አናጣም። በወቅታዊ ችግሮቻችን ላይ እንደትልቅ ተግዳሮት የሚነሳው የትብብር መንፈስ ማጣት ነው። ኢትዮጵያ የአንድና የሁለት ሰዎች ንብረት የምትመስለን አለን። ታሪክ ስናወራ ስለአንድና ሁለት ሰው የምንመሰክር የሚመስለን አለን። ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት። ታሪኩ፣ ባሕሉ፣ ሥርዓትና ወጉ የጋራችን ነው። በችግሮቻችንም ላይ በጋራ መክሮ በጋራ መፍትሔ ማምጣት ግዴታችን ይሆናል፡፡

የሀገራዊ ምክክር ዋና ዓላማ በጋራ ምክር ኢትዮጵያዊነትን መመለስ ነው። በአንድ ሀሳብ፣ በአንድ መድረክ አንድነትን መፍጠር ነው። የደበዘዙ ማንነቶቻችንን ማድመቅ፣ የፈዘዙ ጸዳሎቻችንን መመለስ ነው። ውይይቶቻችን አንድነትን እንዲሰጡን፣ በአንድነታችን ኢትዮጵያዊነትን እንድንመልስ ሠላም ፈጣሪ በሆነ የተግባቦት ሀሳብ ማዋጣት አለብን፡፡

እነሶቅራጠስን ጨምሮ የዚህና የዛኛው ዘመን ታላላቆቹ ፈላስፎች ሠላምን የምንም ነገር መጀመሪያ አድርገው ነው የሚናገሩት። በመንፈሳዊ አስተምህሮትም ብናይ ተመሳሳይ ነገርን እናገኛለን። በተቃራኒው እንደጥላቻና መቧደን፣ የእኔ የአንተ እንደመባባል በሰው ልጅ መካከል አስከፊ ደዌ እንደሌለ የሚናገሩም ጥቂቶች አይደሉም።

በታላቋ ሀገር ስም ስለታላቁ ሕዝብ ስንል ተቻችለን ልዩነቶቻችንን ውበት አድርገን መመላለስ ያስፈልገናል ። ያልተደማመጥንባቸው እነዛ የእልህና የማንአለብኝነት ጊዜያቶች ዛሬን ወልደው ትውልዱን መከረኛ አድርገውታል። መዳኛችን በሰከነ መንፈስ ቁጭ ብሎ መነጋገር ነው። መዳኛችን የችግሮቻችንን ምንጭ በማድረቅ ሌላ አዲስ የተሐድሶ ቦይ መቅደድ ነው፡፡

ሀገር ሰውና ትውልድ በፍቅር ጀምረው በፍቅር ካላበቁ ትላንት እንጂ ነገ የሌለው ግማሽ ባለታሪኮች ነው የሚሆነው። ሙሉ ታሪክ ከሙሉ ገድል የሚጀምር ነው። ሙሉ ገድል ደግሞ ፍቅርና አብሮነት፣ እርቅና ውይይት የታጨቁበት የመንፈስ ከፍታ ነው። ሰውነት ፍጹምና አልተሰጠውም። የሆነ ቀን በሆነ ምክንያት ቅያሜ ሊኖር ይችላል። ቅያሜዎቻችን ጦር እስኪያማዝዙንና ሌላ ቅያሜን እስኪፈጥሩ መጠበቅ ሳይሆን ለምን? በሚል ምክንያታዊ መጠየቅ መልስ መስጠቱ ነው ባለሞገስ የሚያደርገው፡፡

የታሪክ ዶሴዎቻችን ምንም ገድል እንዳልጻፉ አናቸውን መታየታቸው፣ የአብሮነት ሰንደቆቻችን ምንም ጀብድ እንዳልሰቀሉ ባዷቸውን መቆማቸው በእኛ ተለያይቶ መቆም ነው። የታሪክ ምኩራቦቻችን ምንም ገድል እንዳልሠሩ ኮስሰው መታየታቸው፣ የነፃነት አልፋ ደሴት አድማሶቻችን ድር አድርቶባቸው መታየታቸው በእኔና በእናንተ ይዋጣልን እልህ ነው፡፡

መሻቶቻችን ከነመልሶቻቸው መዳፋችን ስር ነው ያሉት። እስከተመካከርን ድረስ፣ ለውይይት በራችንን እስከከፈትን ድረስ የትኛውም ተንኮል፣ የትኛውም ጥላቻ ዝቅ አያደርገንም። ባለመነጋገር ደጃዝማችነታችንን ከተነጠቅን ቆይተናል። ለዛውም የሀገርን፣ ለዛውም የትውልዱን ደጃዝማችነት። መቼ ነው በዝምታ ማልጎምጎም የሚበቃን? መቼ ነው ቆይ ካልሠራሁለት የሚለቀን? እንደሀገር የመቀጠል ዕጣ ፈንታዎቻችን በእጃችን ውስጥ ነው..እንነጋገር፣ እንወያይ፣ በጋራ ለጋራ እንትጋ፡፡

”የጥበብ መጀመሪያ ፈጣሪን መፍራት ”እንደሆነ ሁሉ የሕይወት መጀመሪያም ተነጋግሮ መግባባት፣ ተግባብቶ አብሮ መኖር ነው። በሠላም እጦት የከፈልነው መስዋዕት ዳግም እንዲመጣ በማይሻ መንፈስ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ አለ። ጀግኖች የትም አሉ። በሠላም ውስጥ እንደሚወጣ ጀግና ግን ብኩርና የለም። አሁን ላይ እንደሀገር ስለሠላም እየከፈልናቸው ያሉ መስዋዕቶች የሚበረታቱ ቢሆኑም ረጅም ርቀት እንዲጓዙ ከመሥራት አኳያ ግን የሚቀረን አለ፡፡

ትውልዱ በሀገሩ አፉን እንዲፈታ እውነት ያነገበ የብዙኃነት ፖለቲካ ያስፈልጋል። እንደሀገር በብዙ የልዩነት እሳቤ ውስጥ ነን። ልዩነቶቻችን ደግሞ ሞትና መፈናቀልን፣ ጥላቻና ጥርስ መንከስን ካልሆነ የሰጡን በረከት የለም። ካለፈው ተምረን አዲስ የአብሮነት ጎዳና አለማቅናታችን በአንድ ሕመም ለሁልጊዜ እንድንሰቃይ አድርጎናል። በሀገራዊ ምክክሩም ሆነ ስለአብሮነት በተከፈቱ ሕዝባዊ መድረኮች ላይ ሰሚና ተናጋሪ፣ አድማጭና ተጋሪ ሆነን ስለሀገራችን አዲስ ተስፋን የምንፈነጥቅበት ይሁን፡፡

ሀገር እንደሰው ናት ሕክምና/ፈውስ ያስፈልጋታል። የሀገር ሸረት፣ የትውልድ ተስፋ በእኔና በእናንተ አሁናዊ አስተሳሰብ ውስጥ የተቀመጠ ነው። ስንስማማ እያከበርናት ነው። ስንግባባ እያነገሥናት ነው። በተቃራኒው ስንገፋፋና ስንጠላላ ለማናችንም እንዳትሆን እያደረግናት ነው፡፡

ይሄ ሁሉ ማኅበራዊ ጉስቁልና፣ ይሄ ሁሌ ኢኮኖሚያዊ ድቀት የመጣብን ባለመነጋገራችን ነው። የለመድነው ጠመንጃ መወልወል እንጂ ጉሮሮ መሞረድ አይደለም። መከራዎቻችን እንዲያበቁ ገዳይ መሣሪያዎቻችን አፈሙዛቸውን አዘቅዝቀው ቀና ወደማይሉበት ያሸልቡ። በጦርነት ውስጥ የሚገኝ ሠላም የለም። ሠላም ስፍራው በውይይት ውስጥ ብቻ ነው። በታሪክ የሚባላ፣ በብሔር ካባ የተደበቀ ፖለቲከኛ ሀገር ማቅናት አይችልም።

ሀገር ከጎደፈች ሕዝብ ነው የሚጎድፈው። ሕዝብ ከጎደፈ ሀገር ነው የሚጎድፈው። ችግሮቻችን ሳይገሉንና ሳንገልባቸው በእርቅ የምንፈታበት ጥንተ ጥበብ ያስፈልገናል። ለአንድነት እንትጋ እንጂ በሸንጎና በሸምግልና፣ በጎሜና በይቅር ለእግዜር ስንቱን ያረቀ ማንነት ፍርድና ሚዛናዊነት ይርቁታል ተብሎ አይታሰብም።

የዚህ ዓለም ታላላቅ እውቀቶች መነሻ ስፍራቸው ሀገርና ሰው ነው። ሀገርና ሰው..ሰውና ሀገር ከየትኛውም ምድራዊ ኃይል በላይ ጉልበታም ናቸው። በየትኛውም ሊቃውንትና ፈላስፋ ዘንድ ቅቡልነት አግኝተው ከትላንት ወደዛሬ የመጡ ሁለት ማንነቶች ናቸው። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ቁርሾ ሳይፈጥር ያለፈ ፖለቲከኛ የለም። ባይፈጥርም ትርክት ፈጥረን ስም ማጥፋት እንችልበታለን። እኛም ፖለቲካውም መስተካከል ያስፈልገናል፡፡

የትኛውም ሀገራዊና ማኅበራዊ ተግዳሮት ከውይይት በላይ አይሆንም። በሀገራችን ገላ ላይ ከዛም ከዚህም የተለጎዱ የዘርና የብሔር፣ የጥላቻና የመለያየት ቅርሻቶች እንዲጠሩ ከምንም በላይ እርቅ ተኮር የውይይት መድረክ በስፋትና በጥራት ያስፈልጋሉ። ችግሮቻችንን በጋራ ቀርፈን ወደፊት እስካልሄድን ድረስ ቀና የሚያደርገን ኃይል አይኖርም፡፡

# ስፖርት





## ታዳጊ ቡድኑ ነገ ደቡብ አፍሪካ ላይ ጨዋታውን ያደርጋል

**ብርሃን ፈይሳ**

በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት መጨረሻ በዶሚኒካን ሪፐብሊክ አዘጋጅነት የሴቶች ከ17 ዓመት በታች የዓለም ዋንጫ ይካሄዳል፡፡ በዚህ ውድድር ላይ ከስድስቱ አህጉራት የተወጣጡ 16 ቡድኖች የሚካፈሉ ሲሆን፤ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በሦስት ሃገራት ይወከላል፡፡ ኮንፌዴሬሽኑን ለመወከልም 25 ሃገራት ብሔራዊ ቡድኖቻቸውን በማጣሪያ ጨዋታው በማሳተፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ቡድኖች መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያም የሁለተኛ ዙር የመልስ ማጣሪያ ጨዋታዋን ከደቡብ አፍሪካ ጋር ነገ በፕሪቶሪያ ታከናውናለች፡፡

ቡድኑ የሁለተኛ ዙር የማጣሪያ ጨዋታውን አዲስ አበባ ላይ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ከደቡብ አፍሪካ አቻው ጋር በማድረግ በአሸናፊነት ማጠናቀቁ የሚታወስ ነው፡፡ በአሠልጣኝ ራውዳ አሊ እየተመራ ከታኅሣሥ ወር መጨረሻ አንስቶ በአዲስ አበባ ስታዲየም እና አበበ ቢቂላ ስታዲየም ዝግጅቱን ሲያደርግ የቆየው ቡድኑ ለ26 ቀናት በክፍል ውስጥ እና በመስክ የታገዘ ልምምድ በማድረግ ነበር የመጀመሪያውን ጨዋታውን ያከናወነው፡፡ ቡድኑ በመጀመሪያ 35 ተጫዋቾችን በመጥራት ለቀናት በተደረገው ልምምድ 25 ተጫዋቾችን በማስቀረት ቀጥሎም በልምምድ ሂደት አምስት ተጫዋቾችን በመቀነስ 23ቱን መያዝ ውድድሩን ጀምሯል፡፡

ከደቡብ አፍሪካ ጋር ከነበረው ጨዋታ አስቀድሞም ሁለት የወዳጅነት ጨዋታዎችን ከመቻል እና ከልደታ ክፍለ ከተማ ጋር ማድረግ ችሏል፡፡ ከቀናት በፊት አዲስ አበባ ላይ በአበበ ቢቂላ ስታዲየም በተከናወነው ጨዋታም ኢትዮጵያ 3 ለምንም በሆነ ፍጹም የበላይነት ማጠናቀቋ የሚታወስ ነው፡፡ ቡድኑ በደጋፊው ፊት ያስመዘገበው ይህ ውጤት ቀጣዩን ዙር ለመቀላቀል መልካም አጋጣሚ እንደሚፈጥርለት ይታመናል፡፡ ነገ ፕሪቶሪያ ላይ ለሚያደርገው የመልስ ጨዋታ ዝግጅቱን ሲያደርግ የቆየው ቡድኑ ትናንት ረፋድ ላይ ጉዞውን የጀመረ ሲሆን፤ ከ5 ሰዓት በረራ በኋላ ውድድሩን ከሚያደርግበት ስፍራ ደርሷል፡፡



**ቡድኑ ውጤቱን ማስጠበቅ ከቻለ በየካቲት ወር መጨረሻ የቀጣይ ዙር ጨዋታውን ከኬንያ ጋር ያከናውናል፤**

አራት ዙሮች ያለው የማጣሪያ ውድድሩ በደርሶ መልስ ጨዋታ አሸናፊ በመሆን እስከመጨረሻው የሚጓዙ ሦስቱን ቡድኖች ብቻ በዓለም ዋንጫው ያሳትፋል፡፡ ከእነዚህ ቡድኖች መካከል አንዱ ለመሆን እየተፎካከረ የሚገኘው ቡድኑ የመጀመሪያውን ጨዋታ ባደረገ በማግስቱ ነበር ወደ ዝግጅቱ የተመለሰው፡፡ አጠቃላይ የቡድኑን ቁይታ በተመለከተ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አስተያየት የሰጠችው ዋና አሰልጣኟ ራውዳ አሊ፤ ቡድኗ እሁድ ዕለት የመጀመሪያ ጨዋታውን ካደረገ በኋላ ለመልሱ ጨዋታ የሚሆነውን ዝግጅት በማግስቱ ሰኞ የጀመረ መሆኑን ጠቁማለች፡፡

ቡድኑ በሜዳው በነበረው ጨዋታ የታዩ ክፍቶችን መሠረት ያደረገ ልምምድ በመሥራት ዝግጁ በመሆንም ወደ ደቡብ አፍሪካ አቅንቷል፡፡ ቀደም ሲል ከተመረጡ 23 ተጨዋቾች መካከል ቤዛዊት ንጉሤ ለመጀመሪያ ጨዋታ በፓስፖርት ምክንያት ያልተካተተች ቢሆንም የፖስፖርቱ ጉዳይ ተጠናቆ ከቡድኑ ጋር መቀላቀል ችላለች፡፡ ከዚህ ባለፈ ሁሉም የቡድን አባላት በጥሩ ጤንነት፣ መነቃቃትና ሞራል ላይ የሚገኙ በመሆኑ 23ቱም ተጫዋቾች ለመልሱ ጨዋታ ወደ ስፍራው እንደተጓዙም አብራርታለች፡፡

በደርሶ መልሱ ጨዋታ ኢትዮጵያ አሸናፊ የምትሆን ከሆነ በሦስተኛው ዙር ጨዋታ ከጎረቤት ሃገር ኬንያ ጋር የምትገናኝ ይሆናል፡፡ በማጣሪያው ምድብ ሁለት ከዴሞክራቲክ ኮንጎ ጋር የተደለደለው የኬንያ ከ17 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድን በጨዋታው እንደማይሳተፍ ባሳወቀው ተጋጣሚው ምክንያት በቀጥታ ወደቀጣዩ ዙር ማለፉን ያረጋገጠው አስቀድሞ ነው፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት ህንድ ላይ በተደረገው የዓለም ዋንጫ፤ እንዲሁም ከዚያ ቀደም በ2018 ኡራጓይ ላይ ቻምፒዮን በመሆን ዋንጫውን ያነሳችው ስፔን ናት፡፡ በዚህ የዕድሜ እርከን ጠንካራ ቡድን መመስረት የቻለችው ስፔን ውድድሩ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ጠንካራ ተፎካካሪ መሆኗን እስከ ግማሽ ፍጻሜ በመድረስ አስመስክራለች፡፡ በዚህ ውድድር አፍሪካን ከወከሉ ሃገራት ደግሞ ረጅም ርቀት መጓዝ የቻሉት ጋና እና ናይጄሪያ ናቸው፡፡ የጋና ብሔራዊ ቡድን ትልቁ ውጤቱ እአአ በ2012 አዘርባጃን ላይ በተካሄደው ውድድር ሦስተኛ በመሆን ያጠናቀቀበት ነው፡፡ በተመሳሳይ በሴቶች እግር ኳስ ስመጥር የሆነው የናይጄሪያ ብሔራዊ ቡድንም እአአ 2022 ላይ የዋንጫ ግስጋሴው በግማሽ ፍጻሜው ቢገታም ለደረጃ በተደረገው ጨዋታ የነሐስ ሜዳሊያ ማጥለቅ ችሎ ነበር፡፡